# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ተተኳሪነት

በ


አይናለም ሞርካ



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ

ሰኔ 2015 ዓ/ም

# አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ተተኳሪነት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


በ

አይናለም ሞርካ

ለአማካሪ

ዶ/ር ግርማ ገብረ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ


ሰኔ 2015 ዓ/ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናልዝምና**

**የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት**

**ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

| | | |
|---|---|---|
| **አማካሪ** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ------------------------------ | ----------------------- | ------------------------- |
| **ፈታኝ** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| ------------------------- | ------------------- | ---------------------- |
| **ፈታኝ** | **ፊርማ** | **ቀን** |
| --------------------------- | ------------------------- | ----------------------- |

## ማረጋገጫ (Declaration)

በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ አፈቻውን በወላይትኛ የፈቱ የግልና የመንግስት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት የጽህፈት ክህል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆሪናልዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የዲህረ ምረቃ መረሃ ግብር ለማስተርስ ዲግሪ ማሚያ ያቀረብኩት ጥናት ከዚህ በፊት በሌላ አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን ፣እንዲሁም የተጠቀምኩባቸው ፅሁፎች በትክክል ዋቢ የተደረጉና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም አይናለም ሞርካ ፊርማ ---------------------------- ቀን --------------------

# ምስጋና

ከሁሉም በማስቀደም ይህን የድህረ ምረቃ ትምህርቴን ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ በጤንነት ለጠበቀኝ ለእግዝአብሔር ክብርና ምስጋና ይገባዋል።

በመቀጠልም ያለመሰላቸት ስህተቶቼን እያረሙ፣ እያበረታቱ እና እያንዳንዷን ነጥብ በጥልቀትና በጥንቃቄ እያሳዩኝ ለጥናቱ ፍሬያማነት እገዛ ላደረጉልኝ መምህሬ እና አማካሪዬ ዶ/ር ግርማ ገብሬ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለጥናቴ የሚሆን መረጃዎችን የተባበሩትን የዱቦ እመቤታችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና መምህራንን እንድሁም የአረካ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችንና መምህራንን ሳላመስግን አላልፍም ።

በመጨረሻም ለመስግናችው የሚወደው ውድ ባለቤተን አቶ ይስሐቅ ጆርጌ እና ውድ ወንድሜን ሮቤል ሞርካ ከጅምር  እስከ ፍጻሜ ድረስ  የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ እያደረጉልኝ ስለቆዩ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።እንድሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆሪናልዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ፤ሥነ ጽሑፍ ና ፎክሎር ትምህርት ክፍል።

## ማውጫ


አጠቃሎ...ix

**ምዕራፍ አንድ** ... 1

**1.1 የጥናቱ ዳራ**... 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ... 2

1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ... 3

1.4 የጥናቱ ዓላማ ... 3

**1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች**... 4

1. 6 የጥናቱ ወሰን ... 4

1.7 የጥናቱ ዉሰንነት

1.8 የቁልፍ ቃላት ብያኔዎች

ምዕራፍ ሁለት... 5

ክለሳ ድርሳናት ተዛማች ጥናቶች ቅኝት... 6

2.1 የጽሑፍ ክሂል ምንነት... 6

2.2 የጽህፈት ክሂል አስፈላጊነት... 7

2.3 የመጻፍ ክሂል አላማ... 9

2.3.1. የጽህፈት ትምህርትን አስቸጋር የሚያደርጉ ተለውጦች... 11

2.3.2. የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን ... 12

2.3.3 ሥነ-ልቦናዊ ስነ-ልሳናዊ እና አእምሯዊ ባህሪያት ... 12

2.4 የፅህፈት ክሂል አቀራረቦች... 13

2.4.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ... 13

2.4.2 ሂደታዊ አቀራረብ... 15

2.5 የፅህፈት ክሂል ትምህርት ክውን ስልቶች ... 16

2.5.1 የቁጥጥር ፅሀፈት ትምህርት ክንውኖች (Controlled Writing) ..................................... 16

2.5.2 የምሪት ፅሀፈት ትምህርት ክንውን........................................................................ 17

2.5.3 ካርታዎች፣ ግራፎች፤የስታስቲካዊ ዳታዎችን በጽሁፍ ተንትኖ የማቅረብ ክንዉን ............ 18

2.5.4 መልሶ ምገባ መስጠት (Feedback) ....................................................................... 18

2.6. የጽሀፈት ክህልን ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎች አዘገጃጀትና አደረጃጀት ........................... 19

**2.7. ሥነ-ልቦናዊ እና አእምሯዊ ባህሪያት** ....................................................................... 19

2.8. የጽሀፈት ክህል አቀራረቦች ................................................................................... 20

2.9 የጽሀፈት ክህል መልመጃ አይነቶች ......................................................................... 21

2.10 የወጤታዊ አቀራረብ የጽሀፈት ደረጃዎች ................................................................. 21

2.11 የፅሀፈት ክሂልን መመዘን ..................................................................................... 23

2.12 ክሂል መልመጃዎች የአቀራረብ ቅደም ተከተል። ........................................................ 23

2.13 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ........................................................................................ 24

ምዕራፍ ሦስት ........................................................................................................ 25

3.1 የጥናቱ ዘዴ ...................................................................................................... 25

3.2 የናሙና ዘዴ ...................................................................................................... 25

3.2.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ........................................................................ 25

3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ...................................................................... 25

3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ.............................................................................. 26

3.2.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ............................................................................ 26

3.2.5 የመምህራን የናሙና አመራረጥ ........................................................................... 26

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች............................................................................. 27

3.3.1 ለተማሪዎች የተሰጠ ፈተና ................................................................................. 27

3.3.2 የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ .............................................................................. 28

3.3.3 የመምህራን ቃል መጠይቅ ........ 28

3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 28

ምዕራፍ አራት ........ 29

የመረጃ ትንተና ትርጎማ ........ 29

4.1 የተጠኚዎች ዳራ ........ 29

4.2 በተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጽ ትክክለኛ ሆሄ/ ፊደል/ ቅርጽ አጠቃቀም ........ 30

4.3. በተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጽ ተገቢ ቃላት አጠቃቀም ........ 35

4.4.በተጠቀሱ ትምህርት ቤች የሚጉኙ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጽ የሥረዓተ -ነጥብ አጠቃቀም ........ 39

4.5 በተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች የዐረፍተ ነገር አጠቃም ሁኔታ ........ 45

4.6 የሀለት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች መካከል የጽሕፈት መመሳሰል እና ወይም መለያየት መኖሩ ለማረጋጥ ........ 47

ምዕራፍ አምስት ........ 51

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳብ ........ 52

5.2 የመፍትሄ ሀሳብ ........ 53

ዋቢ መጽሀፍት ........ 56

# የሠንጠረዥ መውጫ

## ሠንጠረዥ


ሠንጠረዥ 1፡- የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ......29

ሠንጠዥ 2፡- ተማሪዎችን አንቀጾች የሚያሪሙ መምራን መረጃ......30

ሠንጠረዥ 3፡-የተጠኚዎች የሆሄያት ቅርጽ ግድፈት በተመለከተ ከአንቀጾቻቸውን የተገኘ ውጤት......31

ሠንጠረዥ 4፡-ከተማሪዎች ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የሆሄያት ቅርጽ ተኮር ምላሽ ትንተና......33

ሠንጠረዥ 5፡- የተጠኝዎች ቃላት አጠቃቀም በተመለከተ ከአንቀጾቻቸው የተገኘውን ውጤት......35

ሠንጠረዥ 6፡-ቃላት አጠቃቀም በተመለከተ ከተማሪዎች ምላሾች የተገኘ መረጃ......37

ሠንጠረዥ 7፡-በሁለት ነጥ አጠቃቀም ላይ የተፈፀመ ስህተት መረጃ......39

ሠንጠረዥ 8፡-በነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ላይ የተፈፀመ ስህተት መረጃ......41

ሠንጠረዥ 9፡- በአራት ነጥብ አጠቃቀም ላይ የተፈፀሙ ስህተት መረጃ......42

ሠንጠረዥ10፡-የሥራዓተ ነጥብ አጠቃቀም ከተጠኚ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ......43

ሠንጠረዥ 11፡- የተጠኝዎች ዐረፍተ ነገት አጠቃቀም ስህተት መረጃ......46

ሠንጠረዥ 12፡- በተተኳሪ ተማሪቸዎች መካከል የጽሕፈት ስህተቶች መመሳልና መለያየት......47

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና አላማ በአረካ ከተማ አስተዳደር አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል ችሎታቸው ምን ላይ እንደሚገኝ እና የትኞቹ የተሻለ ደረጃ እንደሚኙ መለየት በንጽጽር መመልከት ነው፡፡ጥናቱንም ከግብ ለማድረስ አጥኝዋ በዋናነት መጠናዊ ምርምር የተጠቀመች ሲሆን በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር ተጠቅማለች፡፡ የመረጃ ምንጮች በተጠኝዎች የተፃፈ ድርሰቶችና የተሞላ የጽሑፍ መጠይቆች ናቸው፡፡ መረጃዎቹም በቁጥር የመረጃ ትንተና በገላጭ ንድፍ አቀራረብ በንጽጽር ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ ጥናቱም ጥቅል ናሙና ዜዴ በመጠቀም 130 ተማሪዎች አፋቸውንበወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቧል፡ ከተጠኝዎቹም 65 የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲሆኑ 65 ተማሪዎች የመንግስት ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ ከጥናቱ ተሳታፉዎች የተሰበሰበው መረጃ በጥንቃቄ ከተተነተነ በኋላ የተገኘው ውጤት በቃላት አጠቃቀምና ምርጫ፣ በሰዋስው አጠቃቀም፣ በአንቀጽ አደረጃጀት፣ በፊደል ቅርጽ አጣጣልና አጠቃቀም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ ሆነው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀምም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡በመሆኑም የጥናቱ ግኝትን መሠረት በማድረግ ሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያላቸውን የክሂል ክፍተት እንዲያጠበ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ በመሆን ተማሪዎች የግልና የቡድን ስራ እንዲሰሩ በማደረግ አንደ ተማሪ ከሌላው እየተማረ የክሂል እውቀት ክፍተታቸውን የሚሞላበትን መንገድ ማመቻቸት ቢቻል የተሻለ ነው፡፡ እንዲሁም መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ጫና ሳይፈጥሩ ተማሪዎቹ በፈለጉት ርዕስ ላይ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያደርጉበት መንገድ ቢያመቻቹ፡፡ መምህራን ተማሪዎች የፃፉትን ድርሰቶች አይተው ችግራቸውን እንዲቀርፉ ግብረ-መልስ መስጠቱ ለተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂል ማደግ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል በሚል ጥናቱ ተቋጭቷል ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የጽህፈት ክሂል ከተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ጥረትን በተከታታይ በክሂሉ መገልገልን በመማሪያ ክፍልና ከክፍል ውጭ ለልምምድ ብዙ ጊዜ ማጥፋትን ይጠይቃል። የመጻፍ ክሂል አእምሮንና አካልን ማቀናጀት የሚፈልግና ከማሰብ ጋር የተያያዘ ተግባር ሲሆን ይዘቱን ፤ቅርጹን ፤ዓላማውንና ተደራሲውን ወዘተ ከግምት ዉስጥ ማስገባትን የሚጠይቅ ሥራ ነው። በጸሀፊውና በአንባቢው መካከል በሌሎች ተግባቦታዊ ክፍሎች እንደምታየው አይነት ፈጣን ምላሽ አያገኝም። በጸሀፊው ድጋፍ ሰጪ ተግባቦታዊ ዘዴዎች ማለት በአካል እንቅስቃሴ ፤በፊት ገጽታ ፤ በድምጽ ከፍታና ዝቅታ የማይጠቀም በመሆኑ ስነ ልቦናዊ፤ ስነ ልሳናዊ፤ ስነ አእምሮአዊ ችግሮች የሚከስትበት ነው ( Byren 1991:4) እነዚህ ባህርያቱ ደግሞ ክሂሉን በመማር ሂደትና ውጤታማነት ላይ የየራሳቸውን ተጽዕኖ እንደሚያሳደሩ መገመት ይቻላል። በጽሕፈት ክሂል የሚያገለግል ክሂል እንዲዳበር ለትምህርቱ ትኩረት መስጠት በቂ ዝግጅትና ልምምድ ማድረግ እንደሚያስፈልግ Norrish (1990, 63) ይገልጻል።

መምህራን የጽሕፈት ክሂልን በማስተማር ወቅት ጽህፈት መማር ማመቻቸትና መከታተል የተማሪዎችን የጽሑፍ ተግባቦታዊ ክህሎት ማዳበር የተማሪዎችን ጽሁፍ ማንበብና መገምገም በአጻጻፍ ሂደት ተማሪዎች በማሰላሰል ፤በማቀድ ፤በማርቀቅና በመከለስ እንድያልፍ ማድረግ እንዲሚጠበቅባቸው Hedge (1991:11) እና Leki (1996:57) ያስገነዝባል። Richards (1990:11) በበኩላቸው እንዳሉት "መምህራን ተማሪዎች ጥሩ ፅሁፍ እንዲፅፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ብቁ የሆነ የመፃፍ ልምድ ለመከተል እንዲችሉ ነገሮችን ማደራጀት እና ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው"ሲሉ ገልጸዋል።

ከላይ ምሁራኑ የገለጹት ሀሳብ የጽህፈት ክሂል ከባድና ረጅም ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ያመለክታል።ከተማሪዎች ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የጽሁፍ ክሂልን ለማዳበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ማከናወን የሚገባቸው ተግባራት እንዳሉ የሚመለከት ነው። እነዚህም ተግባት ደረጃ በደረጃ ተከታታይ ልምድን የሚጠይቁ ናቸው። ልምምዱ የሚተገበረው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህራንና ተማሪዎች መካከል በሚደረገው መስተጋብር ነው።

Byren (1988) እና Narrish (1983) እንደሚሉት የፅህፈት ክሂልን እንደማዳመጥና መናገር በልምድ የሚገኝ ሳይሆን በመደበኛ ትምህርት አውድ የሚማሩት ነው። ስለሆነም ይህንን የክህል ዘርፍ አፈ ፈትም ሆኑ ኢ-አፈ ፈቶች በትምህርት አማካይነት ያገኙታል በማለት ያስገነዘባል።

ለፅህፈት ትምህርት ስኬት የቋንቋ መምህራን ሁኔታ ብቃትና ዝንባሌ የትምህርት ቤት አጠቃላይ ድባብ፣ የመማሪያ ክፍል ሁኔታ፣ የመረጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ የተለያዩ የቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶች በበቂ መኖር፣ የተማረዎች ሁኔታ፣ ዕድሜ ፣የቋንቋ ችሎታ፤ባህል ዝንባሌ ተነሳስኦት ወዘተ የጎላ አስተዋፅኦ አለው።

Celece Murcia (1991:236) "የተማሪዎች የፊደልን ቅርጽ በመለየት ቃላት መሠረታዊ የቃላትን ምርጫ እና አጠቃቀም በማወቅ ሀሳባቸውን በተገቢው ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ማስተላለፍ የሚችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲያውቁ ፅህፈትን ማስተማር ይገባል" ብለዋል። በመሆኑም ጥሩ የመጻፍ ክሂል ለስነ ትምህርታዊ ብቃትና ለተሳካ ውጤት ለተለያዩ ሥራዎች ና ሙያዎች እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ይህ አስፈላጊና ጠቃሚ ክሂል በአማርኛ ቋንቋ ረገድ በአሁኑ ጊዜ ምን ይመስላል? ብለን ስንጠይቅ ክሂሉ በከፍተኛ ደረጃ የደከመ መሆኑን በውል ከምናስተዉለው በተጨማሪ የተለያዩ ጥናቶችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ። ከነዚህም መካከል ባዬ (2000፤Xxvi) "---በየደረጃው እየተመረቁ የሚመጡ ተማሪዎች ተራ ዘገባ (ሪፖርት) ለማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት እንደሌለቸው ነው። ባጭሩ ሀሳብን አሰተካክሎ አረፍተ ነገር የመግለጽ ብቃት የላቸውም" በማለት የጽህፈት ክሂሉን መዳከም አብራርተዋል። በዚህ የተነሳ ከግልና ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአብዛኛዋቹ ወላጆች ዘንድ ያለው አመለካከት የግል ትምህርት ከመንግስት ትምህርት ቤት ተሽሎ እንድሚገኝ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን የመንግስት ትምህርት ቤት እንደሚሻል አደርገው ይመልከታሉ፤ ይህ ሁኔታ ከተማሪዎች የጽፈት ክሂል ችሎታ ጋር ምን ያህል እውነት ነው የሚለውን ለማረጋገጥ ጥናቱ ይካሄዷል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝዋ ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሳት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂሎቻቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በምን ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ካላት ስራ ልምድና ካጋጠማት ችግር በመነሳት ጥያቄው ይመላለስባት የነበረ ሲሆን፤ ሌላው ምክንያት በግል ትምህርት ቤት ሆነ በመንግስት ትምህርት

ቤት ለመስራት ባገኘችው እድል መሰረት አፋቸውን በወላይተኛ ቋንቋ የፈቱ የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ችግሩ በየትኞቹ ተማሪዎች ላይ ይስተዋለላል ? በጽፈት ክሂል የትኞቹ ይሻላሉ? በዚህ መነሻ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በተጨማሪ ወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር በግል እና በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚኖሩ ተማሪዎች የተኞቹ የተሻለ የጽፈት ትምህርት ክሂል እንዳላቸው ንጽጽራዊ ጥናት ማካሄድ አስፈላግ እንደሆነ በመገመት እንድትሰራ አነሳስቷታል፡፡

በዚህ መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመስ ይሞክራሉ፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የምመልሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉ ናቸው

1. በደቡብ ብሔር/ብ/ህ/ክ/መንግስት በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ አፋቸውን በወላይኛ ቋንቋ የፈቱ የግል ና የመንግስት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምን ምን ናቸው?

2. በደቡብ/ብ/ህ/መንግስት በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ አፋቸውን በወላይተኛ ቋንቋ የፈቱ ከግልና ከመንግስት ትምህርት ቤቶች በዘጠነኛ(9) ክፍል ተማሪዎች ስህተቶቹ ጎልቶ የሚታይባቸው በየትኞቹ ነው?

3. በደቡብ/ብ/ህ/መንግስት በወላይታ ዞን በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ አፋቸውን በወላይተኛ ቋንቋ የፈቱ ከግልና ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ስህተቶችን ባለመፈጸም የተሻሉት የተኞቹ ናችው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና አላማ በአረካ ከተማ አስተዳደር አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት 9ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል ችሎታቸው ምን ላይ እንደሚገኝ እና የትኞቹ የተሸሉ ደረጃ እንደሚኙ መለየት ሲሆን፡-

ሌሎች ዝርዝር አላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የሆሄያት ቅርጽ ስህተቶችን መለየት
- በተጠሱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጻፉት ጽሑፍ ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶችን መተንተን
- የተጠቀሱት  ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የተጠቀሟቸውን ስርዓተ ነጥቦችን በመፈተሽና ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር መጠቀም ያለመጠቀማቸውን መለየት
- በሁለት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች መካከል የችሎታ መመሳሰል እና ወይም መለያየት መኖሩን ማረጋገጥ ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት ተጠንቶ ሲጠናቀቅ የሚከሉት ጠወሜታዎች ተብሎ ይታሰባል፡፡

- አፋቸውን በወላይተኛ ቋንቋ የፈቱ የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማዎች የጽህፈትክህል ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደለ ለመምህራኑ ፍንጭ ይሰጣል፡፡
- መምህራን ባኙት ፍንጭ ላይ በመመርኮዝ የማስተማር ዘዴዎቻቸውን ለማየት እና ለማሻሻል እገዛ ያደርጋል፡፡
- በትምህርት ሂደት ያሉት ችግሮች አጥንቶ የመማር ማስተማር ሂደቱ ሊሻሻል የሚችልበትን መንገድ ይጠቅማል፡፡
- ከመንግስት እና ከግል ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል ችሎታ የተሻለውን መርምሮ ለሌሎች ትምህርት ቤቶች ተሞክሮ ትምህርት ለመስጥት ይጠቁማል፡፡
- በተመሳሳይ መስኩ ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶችም እንደመነሻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1. 6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአረካ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ አንድ የመንግስት እና አንድ የግል ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ያተኩራል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዉስንነት

ጥናቱ በመንግስትና በግል የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጸህፈት ትምህርት ክሂል ላይ ያላቸውን የችሎታ ደረጃ ለይቶ ይጠቁማል እንጂ ለጽህፈት ትምህርት ማስተማሪያነት የቀረቡ ይዘቶችን ፤ክንውኖችን ፤የመልመጃ ተገቢነታቸውን የሚመዝን እና የሚገመግም አይደለም፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላት ብያኔዎች

**ቅርጽ**፡-በአግባቡ ሀሌ ነገር እኩል በሆነ ሁኔታ ተስተካክሎ የተሰራ የተጻፈ  እና የተሳለ ነገር ነዉ

**ንጽጽር** ፡-ሲባል አንድን  ነገር ከአንዱ ጋር ማወዳደር ወይም  ማበላለጥ ይሆናል
**የዕርስ በርስ ትስስር** ፡-ሲባል ደግሞ አንድ ሀሳብ ከሌላዉ ጋር ያለዉ ግንኙነት ወይም ህብረት ነዉ

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት ና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1 የጽሑፍ ክሂል ምንነት ጽንሰ ሀሳብ

ጽህፈት አንዱ የመግባቢያ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን መልክት ተቀባዩና መልዕክት ላኪው በወረቀትና በብዕር አማካኝነት መልእክት ይለዋወጣሉ። ጽህፈት በድምጽ ምልክቶች ሃሰብን በወረቀት ላይ በመስፈር ከሌላ አካል ጋር ለመግባባት ያስችላል። ጽህፈት ከንግግር ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው፤ አንድ ሰው የሚናገረው ለመናገር ሲል ብቻ እንደማይሆን ሁሉ የሚጽፈውም ለመጻፍ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ጋር ለመግባባት እንደሆን በመግለጽ Widdowson (1985:61) የጽህፈትን መግባቢነት አጠናክረውታል።

Byren (1991:61) በበኩላቸው ጽህፈት የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ትዕምርቶች ተጠቅሞ ሀሳብን በወረቀት ላይ የምናሰፍርበት ሂደት ነው። ንግግር ድምጽ ከማመንጨት በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም ትዕምርቶችን በመጠቀም ቃላትን ፤አረፍተ ነገሮችን አንቀጾችን ወዘተ ለቋንቋው ስርዓት መሰረት አቀናብሮ የሚያቀርብ ነው ብለዋል። Haremer (1991;16) እና Zamel (1985;97) ደግሞ የአንድ ቋንቋ ድምጾች ከሚወክሏቸው ምልክቶች ጋር እየተዛመዱ በወረቀት ላይ በመስፈር መልዕክት የሚተላለፍበት ክሂል ነው በማለት ገልጸዋል።

በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂል አካልና አእምሮን በማስተባበር ድምጾች በምልክት በመወከል ሀሳብን ለአንባቢ የምናቀርብበት ክሂል ነው። በጽሑፍ የሰፈረን ሀሳብ የሚከታተል አንባቢ ደግሞ መልዕክቱን በትክክል የሚረደው ጽሁፍ የቋንቋውን ስርዓት የጠበቀ እንደሆነ ብቻ ነው።

በዚህ መንገድም ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል።ጽሁፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተደረጉት ሙከራዎች ያዳጋል፤ ይዳብራል፤ ይበለጽጋል።

የሻው (1996፤20) "ጽሁፍ መረጃዎች ፤ታርክን ፤እውቀትና የፍልስፍና ቅርሶች እየሰነደ ከተውልድ ወደ ትውልድ በማስተማር በትናንቱና በዛሬው በነገው ትውልድ መካከል መቀራረብን ወይም ግንኙነትን ይፈጥራል። ይህ አገላለጽ ጽህፈት ያለፈው የአሁኑንና የወደፍቱን ትውልድ

ያፈራቸውንና የሚያራቸውን ትሩፋቶችንና ቅርሶችን እየሰነደ ከአንዳቸው በማስተላለፍ የእርስ በርስ ትስስር እንድኖራቸው በማድረግ ሂደት ከፍተኛ እገዛ እንዳለው ያሳያል፡፡

ጽህፈት ከተግባር ጋር ጥልቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተደጋጋሚ በሚካሄዱ ሙካራዎች ያድጋል፣ ይዳብራል፣ ይበለጽጋል፡፡ እንደByrne (1988:1) Norrish (1983:6) የጽህፈት ትምህርት ሂደታዊ እንጂ ቅፅበታዊ ያለመሆኑን በመግለፅ ተማሪዎች ረጅም ጊዜን በመውስድ ልምምድ በማድረግ የፅህፈት ክሂልን ማዳበር እንደሚችሉና የሚያደርጉትን ልምምድ ሂደታዊ መሆኑንም በተጨማሪ ያስገነዝባል፡፡

ሰለሞን (1991፡7) Zamel (1992)ን በመጥቀስ መጻፍ ሂደታዊ ከመሆኑ ባሻገር ዓላማ ያለው ( Purposeful) እያደረገ የሚሄድ (Evolutionary) ድግግሞሽ ወይም ተመላላሽነት ያለው (Recursive) ምልልምስ (Dialogic) ፈሳሴ ( Fulid) ) እና አሳሽ (Explatory) እንደሆነ ገልጽዋ ፡፡

ይህ አገላለጽ ሰው በጽህፈት በኩል ይማራል ፣ያስባል ፣እውቀትንም ገንዘቡ ማድረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪ ጽህፈት አዲስ ሃሳብን የማመነጨት ዘዴ በመሆን ሀሳብን በሚታይና ቋሚ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላለፍ ምሁራን እውቀታቸውን እንዲያንጸባርቁበት በማህበራዊ ህይወትም ውስጥ ማስታዎሻ ለመያዝ ደብዳቤ ለመጻፍና ሪፖርቶችን ለማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 2.2 የጽህፈት ክሂል አስፈላጊነት

የጽሕፈት ትምህርት ከንባብ ጋር በጣም የተቆራኘ ግንኙነት አለው፡፡ የነዚህ የሁለቱ ክሂሎች ቀዳሚ ተግባር ፊደል ከማስለየት ይጀምራል፡፡ የምናነበው በፊደል የተገነባ ነገር ነው፡፡ የምንጽፈውም በፊደል ነው፡፡ ስለዚህ የጽህፈት ትምህርት መጀመሪያ የሚያስገኘው ጥቅም በቋንቋ ውስጥ ያሉ ድምጾች የሚወክሏቸውን ምልክቶች መለየት ነው፡፡ምንም እንኳ ፊደልን የማስለየት ተገባር የመጀመሪያው የጽህፈት ትምህርት አላማዎች ትግበራ በተማሪዎች እድሜ፣የትምህርት ደረጃናፊላጎት መሰረት በተለያዩ ደረጃዎች የጽህፈት ትምህርት አላማ ሊለያይ ይችላል፡፡

የጽህፈት ክሂል ከአራቱ ቋንቋ ክህሎት አንዱ ሲሆን የማመንጨት ክሂል በመባል ከመታወቁም በላይ የጽህፈት ክሂል የቋንቋ ተጠቃምዎች ጥቅል ክሂሎች በአንድ ጊዜ እንደኖራቸው

ያደርጋል፡፡ለዚህም የጽህፈት ክህል ዋነኛውና ተጠቃሽ ምሳሌ ነው፡፡ በማለት Haremer (1991) የጽህፈት ክህል በባህሪው ክሂለ ብዙ ነው፡፡ የሀሳብ አደረጃጀት የአንቀጽ አመሰራረት ፤ዐረፍተ ነገር አወቃቀር፤ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ለመጻፍ ክሂል ትምህርት ከሚያስፈልጉ ክህሎች መካከል በቀዳምነት ይጠቀሳል፡፡

እንደማሪው (1998፡164-165) ገለጻ የመጻፍ ክሂል እየጻፉ መማርንም ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቀጥታ ወደ መጻፍ ስራ ከመግታቸው በፊት በሂደቱ ላይ ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል በማለት ለአብነት የሚከተለትን ሂደቶች በቅደም ተከተል ማለፍ እንደሚኖርባቸው ይዘርዝራሉ፡፡

- ለምን እንደሚጻፍ በውል መገንዘብ ፡
- ለማን እንደሚጻፍ ለይቶ ማወቅ፡
- በምልከታ በማስታወሻ በመመዝገብ እርስ በርስ በመወያየትና በማንበብ አስፈላጊ መርጃዎችን ማሰባሰብ፡
- እንደት መጻፍና መረጃዎችን እንደት ማደራጀት እንደለባቸው የሥራ እቅድ ማውጣት፡
- የመጀመሪያ ረቂቅ መንደፍ፡
- ረቂቁን መገምገም ፤መከለስ፤
- በርካታ ረቂቆችን እንደት በተደጋጋሚ ካዘጋጁ በኋላ የመጨረሻውን ጽሁፍ መጻፍ፤
- ለመጨረሻ ጊዜ እንደገና በጥልቀት አንብቦ መገምገም፡፡

የትምህርት ደረጃና ፍላጎት ባላቸው ችሎታና ልምድ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ እነዚህ ነገሮች ግምት ውስጥ ከግቡ ወደ ግብ ለመድረስ መስናክል ሊሆን እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡ በየክፍሉ ደረጃው የሚሰጠው ጽህፈት ትምህርት ዓላማና የሚያስገኘው ጥቅም የተለያየ ነው፡፡ በዝቅተኛ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች የፊደላት ቅርጽ በመለየት ቃላትን መመሰረት፤ የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማወቅሀሳባቸውን በተገቢ ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች መግለጽ የሚችሉበትን የተግባቦት ስረዓት እንዲያወቁ የጽህፈት ትምህርት ከዚህ ሌላ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ላሉ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግና ስርዓት ጠብቀው ሀሳባቸውን በተገቢው መንገድ እንዲገልጹ ያስችላል እንዲሁም ለማስተላለፍ የፈለጉትንም መልእክት እነሱ እንዳሰቡትና እንተረዱት በትክክል የሚያቀርቡለትን አካል ተገቢ ቃላት ፤ ዐረፍተ ነገሮችና የተዋጣለት አንቀጽ የጽህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ በመሆኑም Heaton (1990:14) የጽህፈት ትምህርትን በመማር የሚከተሉትን ችሎታዎች ማዳበር እንደሚቻል ዘርዝርዋል፡፡

1. የሰዋሰው እውቀት፦ የቋንቋውን ህግነና ስርዓት የጠበቁ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቶ ለአንባቢ ግልጽና ትክክለኛ መልእክት ለማስተላለፍ የሚያስችል ብቃት እንዲኖር የፅፍት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

2. የስልታዊነት ክሂሎች ፡- ስልታዊነት ማለት አንድ ፀሀፍ የሚከተለውን የአፃፃፍ ዘዴ የሚያሳዩ ነው፡፡ በመሆኑም የተሰማውን ውስጣዊ ስሜት ለመግለጽ የሚያስችሉ ቃላትን አመንጭቶ የመፃፍ ችሎታ እንዲኖረው የፅህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

3. የአፃፃፍ ስርዓት ክህሎች ፡- የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት በመጠቀም በተገቢው ሁነታ የመጠቀም ችሎታ እንዲኖር የፅህፈት ትምህርት ያግዛል፡፡

4. የአጠቃቀም ክሂሎች፦ ተገቢውን ቃላት ለተገቢው ቦታ በመምረጥ የማቅረብ ችሎታና ሃሳብን በትክክል በማቀናጀት የመፃፍ ብቃት እንዲኖር የፅህፈት ትምህርት ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡

ይህም ማለት የቃላት አጠቃቀማችን የተደራሲያንን እድሜ፣ ፍለጎት፣ ባህል የኑሮ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃና የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

የፅህፈት ትምህርት የተለያዩ የመማር ስልቶችንና ፍላጎቶችን ለማስገኘት እንደሚረዳ፣ የተለያዩ ክህሎች በማቀናጀት መማር እንደሚያስችልና መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ፈተናዎችን ለማቅረብ እንደሚያገለግል ተብራርቷል፡፡ እንዲሁም የጽሁፍ ትምህርት በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ድምጸችን የሚወክሉ የተለየዩ ምልክቶችን ከማሳየት አንስቶ ሀሳብን ተጠየቃዊና ቅድም ተከተካላዊ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ የሚያስችል ብቃትን ያጎናጽፋል፡፡

አጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የፅህፈት ትምህርት የማስተማር ጥቅሞች መሠረት በማድረግ ተጠኚ ተማሪዎች እምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለመመርመር ለጥናቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸውነጥቦች ናቸው፡፡

## 2.3 የመጻፍ ክሂል አላማ

የጽህፈት ትምህርትን የምናስተምሪበት ዋነኛው አላማ ትማርዎች በስልጣኔ እየዳበረ ከመጣው የአላማችን ሁኔታ ጋር ተጣጥመው እንዲሄድ ለምድረግ ይሆናል፡፡

ከትምህሪቱም አላማ ይህንን የጽህፈት ትምህርት ከግብ ለማድረስ የሚያግዝ እና በማስተማሪ ስልቶች ላይ የተመሰረተ ልሆን ይገበዋል በማለት Lee (1997:73-76) ይገልጽዋል፡፡ጽህፈት ተማሪዎች እንድጽፉ ማድረግ ሁለት አላማዎችን ይዞ ይተገብራል፡፡ እነዚህ አላማዎች መጻፌን በተናጠል ማጎልበት እና እግረ መንገዱን ለመጻፌ የሚያግዙን ሌሎች ክህሎችን ማዳበር ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ዋና አላማ እራሱን ጽሁፉን መጻፌ እንድችሉ መድረግ ነው፡፡የመጻፍ ክህል በልምድ የሚገኝ ባለመሆኑ ለተከታታይ ክህሎትነት ተማሪዎች ሊያውቁትና ሊማሩት በሕይወት ዘመናቸው ሊገለገሉበት ይችሉ ዘንድ ለማድረግ ነው (Baskoff 1972:29)

ሁለተኛ አላማ የሚሆነው የጸሁፍ ሥራ ለሌሎች ክህሎች ዋና አጋዥ ሆኖ ማገለገሉ ነው፡፡ የመጻፍ ሥራ ሰዎችን ወይም ተማሪዎችን በግል የመስራት ልምደቸውን ያዳብራሉ፡፡ስለዚህ ተማሪዎች በመስማት ብቻ ላይ አያተኩሩም ፡፡በመሆኑም የጽህፈት ሥራ ለሌሎች ክህሎች ማዳበሪያና ማጠናከሪያ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ለመጻፍ ማደመጥ ፤ ለመጻፍ መናገርል ፤ለመጻፍ ማንበብ አስፈላግ መሆናቸውን ልብ ሊባል ይገባል ፡፡

Abiy (2013:58) "የጽህፈት በሁለተኛ ቋንቋ ለማዳበር የአፍ መፍቻ ቋንቋ የጽህፈት ኪሂል ትልቅ አስተዋጽኦ አለው" በማለት ያብራራል፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመጽሀፍ ትኩረት ሰጥተው ማስተማር በቀጣይ በሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩት የጽህፈት ትምህርት መንገዱን ቀላል እንደሚያደርግላቸው ለማሳየት ነው፡፡

ሃና (2003:9) የጽህፈት ትምህርት ተቀዳሚ አላማ ተማሪዎች በጽሁፍ አማካይነት ሀሳባቸውን በተቃናና በተዋበ መንገድ በመግለጽ ጽሁፋቸው ተግባቦትን እንዲለማመዱ ማስቻል ነው በማለት ይገልጻል፡፡

Hedge (1990:10) እንደገለፁት "ተማርዎች እንዲያቅዱ እንዲያረቁና፤እንዲከልሱ መርዳት የመምህሩ እኩልታ ተግባር ሲሆን በጽህፈት ሂደታቸው የሚያስፈለጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች የፅህፈት ክሂልን ለመጨበጥ በሚያደርጉት በርቱ ጥረት የሚረዳቸው ድጋፍ ማግኘት ይፈለጋል፡፡

የሚያስፈለጋቸውን አዎንታዊ ድጋፍ እንድያገኙ ማድረግም በራስ መተማመንን እንዲያዳብራቸው ይረዳቸዋል፡፡ከተማሪዎች ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የጽሁፍ ክሂልን ለማዳበር

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ማከናውን የሚገባቸው ተግባራት እንዳሉ የሚመለክት ነው። እነዚህ ተግባራት ደረጃ በደረጃ ከተከታታይ ልምድን የሚጠይቅ ናቸው።ልምምዱ የሚተገብረውበመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህራንና ተማሪዎች መካከል በሚደረደው መስተጋብር ነው።

ይህ ሂደታዊ መስተጋብር ተማሪዎች የዳበረ የጽህፈት ችሎታ እንዲኖራቸው ከመረዳቱም ባሻገር የተነደፈው አላማ ግቡን እንዲመታ እገዛ ያደርጋል።በእንጻሩ ደግሞ የአተገባበር ችግር ካለበት በተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሰደሩ አይቀረ ነው።ይህንንም ሀሳብ ማጠናከር Richardis ;( 1990; 106) “ውጤታማ የጽህፈት አቀራረብ ዘዴ ትኩረት ተማሪዎች ከስህተት የጸዳ ጽህፈት እንዲጽፉ ማድረግ ነው።” በማለት ያብራራል።

Byren (1988): Norrish (1983) የፅህፈት ክሂልን እንደማደመጥና መናገር በልምድ የሚገኝ ሳይሆን በመደበኛ ትምህርት አውድ የሚማሩት ነው። ስለሆነም ይህንን፣የክሂል ዘርፍ አፈ ፈትም ሆኑ ኢ-አፈ ፈቶች በትምህርት አማካይነት ያገኙታል በማለት ያስገነዝባል። ለጽህፈት ትምህርት ስኬት የቋንቋ መምህራን ሁኔታ ብቃትና ዝንባሌ የትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ድባብ፣የመማረያ ክፍል ሁኔታ፣የመረጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣የተለያዩ የቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶች በበቂ መኖር፣ የተማሪዎች ሁኔታ፣ዕድሜ፣ የቋንቋ ችሎታ፣ባህል፣ዝንባሌ፣ተነሳስኦት ወዘተ የጎላ አስተዋጽኦ አለው።

Celece Murcia, (1991:236) ተማሪዎች የፊደልን ቅርጽ በመለየት ቃላትን መስርተው የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማውቅ ሀሳባቸውን በተገቢው ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ማስፋፋት የሚችሉበትን የተግባቦት ሰርዓት እንዲያውቁ ፅህፈትን ማስተማር በማለት ገልጸዋል።

## 2.3.1. የጽህፈት ትምህርትን አሰቸጋር የሚያደርጉ ተለውጦች

የጽህፈት ክህል አላማው በሁለተኛው ደረጃ ተማሪዎች በጽህፈት ተግባቦት መገለገል እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን ክህሎች ሁሉ አዳብረው ሀሳባቸን በጸሑፍ የመግለጽ ችሎታ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። ይህን ችሎታ ለማስገኘት በሚድረግ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ በርካታ መስናክሎች ይኖራሉ።

ከነዚህ ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ Nunan (1989)፥Hedge (1988); Norrish (1990) እና Richards (1990) ገልጸዋል።

## 2.3.2. የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን

የጽህፈት ክሂል በቀላሉ የሚጨበጥ ክሂል አይደለም ፤ክሂሉ ውስብስብና ሪቂቅ የሆነ ክሂል፡፡በተላይ ደግሞ አስቸጋሪነቱ የሚያጎላው እንማዳመጥና መናገር በልምድ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚነኝ መሆኑ ነው፡፡የጽህፈት ስራ ሀሳብን ከማደራጀት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡አእምሯዊ እና አካላዊ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡ሃሳብን በጽሑፍ ለማስተማር ጊዜ ይወስዳል፡፡

እነዚህ ሁሉ ባህሪሪያቱ ውስብስብነቱንና አስቸጋሪነቱን ያሳያል፡፡ ብዙ ጊዜ ወስዶ ተጽፎም በመጨረሻ ውጤቱ የታሰበውን ያህል የተፈለገውን መልእክት ላያስተላልፍና ላያረካ ይችላል፡፡የጽህፈት ክሂል ሚልክቶችን በወረቀት ላይ ከማስፈር ያለፈ ነገር ነው፡፡ አንዱ የተዋጣለት ጽሐፍ አጠናቅቆ ለማቅረብ ብዙ ነገሮች ማወቅ የጠይቃል፡፡

ከነዚህ ችሎታዎች መካከል የሚከተሉትን Hedge (1988:5) ዘርዝርዋል፡፡

1.ሀሳብንና መረጃዎችን አቀናጅቶ አጠናቅሮ ማቅረብ ፤

2. ከአሻሚነት ነጻ በሆነ መንገድማቅረብ ፤

3. ለአጽንኦት ሲባል ውስብስብ ያሉ ስዋሰዋዊ ሥርዓቶችን አለመጠቀም፤

4. ጥንቃቄ የተሞላ የቃላት ምርጫና አጠቃቀም መከተል፤

5. ተገቢውን የሰዋሰው አጠቃቀም መከተልና የዐረፍተ ነገር መጠን መወስንን መወቅ፡፡

ከላይ የቀረቡት የፅህፈትን ውስብስነት የሚያሳዩ ነጥቦችና ጽህፈትን አጠናቅሮ ለማቅረብ የሚረዱት ነጥቦች ተጠኝ ተማሪዎች በፃፉት አንቀጾች ከተነሱት አምስት ነጥቦች የትኛው ላይ የተሸለ ትኩረት እንዳለባቸው ለማወቅ አስችሏል፡፡

## 2.3.3 ስነ-ልቦናዊ ስነ-ልሳናዊ እና አእምሯዊ ባህሪያት

በጽህፈት ትምህርት ላይ ተጽዕኖ ከተሚያሳድሩት ተለውጦዎች ማከል ስነ-ልቦናዊ ሰነ-ልሳናዊ እና ሰነ-አእምሯዊ ሁኔታዎች እንደሆኑ Byrin (1991): Richarde (1991) እና NOrish (1983) ያስረዳል፡፡በመሆኑም ቀጥለን የተወስኑትን በዝርዝር እንመለከታለን፤-

ሀ.ስነ-ልቦናዊ ባህሪ ፅህፈት የማፍለቅ ተግባር የሚከናውንበት ክሂል እንደመሆኑ መጠን አንባቢ እያሰቡ መፃፍ የማይቀር ነው፡፡ፀሀፊውምመልእክቱም ለአንባቢ ግልጽና ሳቢ በሆነ መንገድ ለማድረስ ሲል ከወዲህ በሐሳብና በጭንቀት የሚሞላበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ይህም የጽሁፈት ክሂልን አስቸጋርሪ ያደርገዋል፡፡ በንግግር ጊዜ ግን ተናጋሪ ወዲያኑ ከአድማጩ ምጋበ ምላሽ የዘገየ ነው (Byren 1991: 4)፡፡

ለ.ስነ-ልሳናዊ ባህሪ፡-በፅህፈት አማካይነት ሀሳብን በሚገባ ለማስተላለፍም ሆነ በዚሀ ቋንቋ አማከይነት ተፅፎ ወይም ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን መልእክት ለመረዳት የቋንቋን ውስጣዊ በህሪ ማወቅወሳኝ ነገር ነው፡፡በንግግር ሂደት ውስጥ ጠቃሚነት የሌላቸውንና የሚንተዋቸውን ሁሉ ደግመን በማለት ወይም እንደገና አሰተካከለን ለማስቀመጥ እድል ስላለን ልናስተካከለው እንችላለን፡፡ይህ ሁኔታ በፅህፈት ጊዜ የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም ስንፅፍ በጣም ተጠንቅቀን፤እና አስበንና ጊዜ ወስደን እያንዳንዱን ቅንጣትአስተካክለን ማቅረብ ይኖርብናል Byreen (1991:4) እና Norrish (1983:42) ፡፡

ሐ. ስነ-አእምሮ ባህሪ፡-ፅህፈት በልምድ ሳይሆን በትምህርት ሂደት የአእምሮን ውስጣዊና ረቂቅ ተግባር የሚጠይቅ ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ጽህፈት እንደደረጃዎችን ፈተናን ለማለፍ አሊያም ለክሂልነት ብቻ የምንማርው ጥበብ አይደለም፡፡ ይልቁንም ትምህርቱ ሌሎች ክሂሎችን ለመማርና ተጨማሪ እውቀቶች ለመቅመስሚያነትም ያገለግላል፡፡ፅህፈት ሀሳብን ከእምሮ አመንጭቶ በወረቀት ላይአስተካክሎ ማስፈር ከባድና አእምሮ ሊፈትን ይችላል፡፡ Byren (1991:4)::

## 2.4 የፅህፈት ክሂል አቀራረቦች

የፅህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በሁለት እንደሚመደቡ የተለያዩ ምሁራን ያመለክታሉ፡፡እነዚህ ውጤት ተኮር አቀራረብና ሂደታዊ አቀራረብ እንዲሆኑ Nunan (1989;30) እና Richarid (1990:106) ይገልፃሉ፡፡

### 2.4.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ

ውጤት ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ ትኩረት ከፅህፈት ሂደትይልቅ ተማሪዎች በሚያፈልቁት የመጨረሻ ውጤት ላይ ነው፡፡ በዚህ አመለካከት የተማሪዎች የመጻፍ ብቃት ከፍ ሲል ውስብስብ የፅህፈት ተግባራትን የመቆጣተር ችሎታን ያዳብራል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ብዙ የተለያዩ

ስልቶችን ይጠቀማሉ፡፡ውስብስብ የአረፍተ ነገርና የአንቀጽ አደረጃጀት ቅንብር ይካናሉ (Richards (1990:108) Nunan (1989:36) ይህ አቀራረብ የፅህፈት ምንነት የሚላካው የሰዋሰው ሕግጋትምተስተካክሎ ከመተግበር አንጻር ሲሆን አይነተኛ ትኩረት በስተመጨረሻ ተጠናቆ የሚቀርበው ስራ ላ አንድ ፅሑፍ እንዴት እንዲሚዘጋጅ የሚፈጽመው ሂደት ላይ አይደለም፡፡ አቀራረብ በአንድ በኩል ተማሪዎች ልዩ ልዩ የፅሁፍ ስራዎችን እንዲያዘጋጁ የሚረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ስህተት እንዳይሰሩ የሚከላከል ነው፡፡(Richards 1990:106) ለቅርጽ ከፍተኛውን ትኩረት በስተመጨረሻ ተጠናቆ የሚቀርበው ሥራ ላይ እንጂ በጽሑፍ እንዴት እንደሚዘጋጅ በሚፈጸመው ሂደት ላ አይደለም፡፡ አቀራረቡ በአንድ በኩል ተማሪዎች ልዩ ልዩ የጽህፈት ሥራዎችን እንዲያዘጋጁ የሚረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ስህተት እንዳይሰሩ የሚከላከል ነው፡፡ (Richarids 1990:106) ለቅርጽ ከፍተኛውን ትኩረት በሚሰጠው በዚህ አቀራረብ ብዙውን ጊዜ ርዕስ በመምህሩ ተወስኖ የሚሰጥ ሲሆን ዐረፍተ ነገር ምሥረታ ባዶ ቦታ መሙላት ፤ዐረፍተ ነገር ማስፋት፣አንቀጽ ማዳበር ወዘተ የተለመዱ ተግባሮች ናቸው፡፡

በውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ሲማሩ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት Pincas (1982:14) ገልጸዋል፡፡

ሀ. የትውውቅ ደረጃ፡- ተማሪዎች ወደ ዋናው የጽህፈት ሥራ ከሚገባታቸው በፍት በመምራቸው የሚቀርብላቸውን ሞደል ፅሁፍ በማንበብ በመራፍ ራሳቸውን የሚያዘጋጅበትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ደረጃ ነው፡፡

እንደ Pincas (1982:14) ገለጻ ለተማሪዎቹ በመምራቸው ተመርጦ የሚቀርብላቸው ሞዴል ጽሁፍ ሊያስነሳሳቸው የሚችል መሆን አለበት፡፡ ከዚህም ሌላ እድሚያቸውን ፣የክፍል ደረጃችውን ፣ባህላቸውንና ጾታቸውውን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡

ለ. የልምምድ ደረጃ፡-የልምምድ ደረጃ ተማሪዎች የተለያዩ ሞዴል ፅሁፎች ጋር ከተዋውቁ በኂላ በራሳቸው ተነሳሽነት የራሳቸውን ሀሳብ እያፈለቁ መፃፍን እንድለማመዱ የያደርግበት ደረጃ ነው፡፡እንደ Pincas (1982:18) ገለጻ ተማሪዎች በልምምድ ደረጃ ውስጥ ፅህፍትን ተለማምደው ቀስ በቀስ ወደ መር የፅህፈት ክንውን ደረጃ የሚሸጋገርበት ነው፡፡

ሐ. የውጤት ደረጃ፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ከላይ ባሉት ደረጃዎች የተለማመዱባቸውን የጽህፈት ስራዎች ወደ ውጤት የሚቀየሩበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎች ያለምንም እገዛ የሚሰጣቸውን የጽህፈት ትምህርት ደስ እንዳላቸው በነፃነት ያከናውናሉ፡፡ የመምህሩ ሚናም

አነስተኛ ነው፡፡እንደ Pincas (1982:21) ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ሀሳባቸውን እያፈለቁ በነፃነት የሚፅፍበት አቅማቸውን የሚያጎለብቱበት ነው፡፡

በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በወረቀት ላይ እንዲያስፈሩ ነው የሚፈለገው ስዋሰዋዊ ትክክለኛነቱ የአንቀጽ አደረጃጀቱ የቃላት አማራረጡ በመጨረሻ ላይ የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

Raimes (1983:7): Hedge (1988:44)::

## 2.4.2 ሂደታዊ አቀራረብ

ተማሪዎች ዉጠት ተኮር አቀራረብን ጽህፈትን በማስተማር ረገድ ድክመት እንዳላቸው በቅርብ አመታት አመልክተዋል፡፡ዉጠት ተኮር አቀራረብ አትኩሮቱን ከማሳደግ ይልቅ መድረስ ላይ ነዉ፡፡ተማሪዉ በህደት የተለያዩ ደረጃዎችን እያለፈ እንዲመጣ ሳይሆን የታሰበዉ ግብ ላይ እንዲደራስ የሚያደርግ አቀራረብ ነዉ፡፡በመሆኑም የጥሩ ጸሀፊዎች ሂደታዊ አቀራረብን ምርጫቸዉ አድርገዋል፡፡

ሂደታዊ አቀራረብ አይነተኛ መገለጫው ፀሀፊው በመፃፍ ሂደት የሚፈፅማቸውን ተግባራት በመግለጽ ላይ ማተኮር ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ በትክክለኛነቱ (accuracy) ምትክ የፀሀፊው የአጻጻፍ ሂደት ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል፡፡ የዚህ ፈለግ አራማጆች ትኩረት የሚያረጉት በመጨረስ ተጠናቆ በሚቀርበው የፅህፈት ውጤት ሳይሆን ወደዚህ ለማድረስ የሚያስችለው ስለፅሁፍ አላማና ስለ አንባቢያን ሳይሆን ፅሁፍን እንዴት ልጀምረው? እንዴትስ አቀናጅቼ ልጻፈው? የሚለው ጉዳይ ላይ ነው Raimes (1983:10)::

በዚህ የጽህፈት አቀራረብ ተማሪዎች ድርሰታቸውን የሚፅህፉት በውጤታዊው አቀራረብ እንደሚዘውተረው በመምህሩ ተሳትፎ በሚሰጣቸው ርዕስ አይደለም፡፡ ራሳቸው የሚሰማቸውን ርዕስ ይመርጣሉ፡፡ የፅሁፋቸው ረቂቅ ለመምህራቸው ሆነ ለጓደኛቸው ያሳያሉ፣የሚያገኙትም ምላሽ የበልጥ እንያስቡበት ይገፋፋቸዋል፡፡

በፅህፈት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉ፡፡የፅህፈት ስራ ያከናወነው ሰው ሊያከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች ለመፃፍ መነሳሳት፣ሀሳቦችን ማገናኘት፣ሀሳቡን በቢጋር መልክ ማዘጋጀት፣ማስታውሻመውስድ፣የመጀመሪያውን ረቂቅ መፃፍ ፣መከለስ፣እንደገና ማቀድ፣ደግሞ ማርቀቅ፣በመጨረሻም ለስህተት ማዘጋጀት በተባሉ ክንዋኔዎች ውስጥ እንደሚያልፍ ያስረዳል፡፡

እነዚህ ክንዋኔዎች በሶስት ዋና ዋና የፅህፈት እርከኖች እንደሚከፈሉ RiChards (1990:112) (Hedge1988:22-24)::

እነሱም፡-1. ቅድመ ፅህፈት (pre-writing)

2. የፅህፈት ጊዜ (while-writing)

3.ድህረ ፅህፈት (post-writing)

## 2.5 የፅህፈት ክሂል ትምህርት ክውን ስልቶች

እነ ሰለሞን (1994) Devid Kros ጠቅሰው እንደገለፁት የፅህፈት ትምህርት ክንውኖች (ስልቶች) የሚባሉት በሶስት የተለያዩ መንገዶች ማቅረብ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡እነዚያ መንገዶች አንድ በአንድ እንደሚተለው ይቀርባል፡፡

### 2.5.1 የቁጥጥር ፅህፈት ትምህርት ክንውኖች (Controlled Writing)

የቁጥጥር ፅህፈት ለተማሪዎች ሃሳባቸው ለመግለጽ ነጻነት የማይሰጥ የፅህፍት ትምህርት መከወኛ ስልት ነው፡፡ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸው ነገር በመምህራቸው ይሰጣቸዋል፡፡ (ዳንኤል 1998፤77)

ቁጥጥር ፅህፈት ውስጥ ከሚካተቱ የፅህፈት ፈተና ስልቶች አይቶ የመገልበጥ ክንውኖች ፤የተሳሳተ ፅሑፍ ሰጥቶ ታርሞ እንድገለበጥ ማድረግ የክሎዝ (cloze) ምንባብ ክንውን ፤የቃል ፅህፈት ክንውን ፤የቅነሳ ክንውን ወተ ናቸው፡፡

ሀ.አይቶ የመገለበጥ ክንወኖች ፡- በዚህ የፅህፈት ክሂል ስልት ተማሪዎች የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ፤የትርጉም ለውጥ እንድፈተር በጥንቃቂ የቃላት አስካክ እንዲጠሙ የደረግበት ነው፡፡

ለ. የተሳሳተ ፅሑፍ ሰጥቶ ታርሞ እንዲገለበጥ ማድረግ ፡-ይህ ክንውን የሚሰጠው በፅሑፍ ሃሳብ ለማቅረብ የሚረዱ የቃላትና የሰዋስው እውቀት እንድኖራቸው በማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡እንደ ክፍል ደረጃው ክንውኖች ቀለልና ጠንከር ያሉ ሊሆኑ ይችላል ፡፡ለምሳሌ አውሮፒላኖች በሰማይ ላይ ሲሽከረከር አየሁት፡፡ የሚለው ዐረፍተ ነገር አስተካክለውና በቃለት መሃል ሊኖር የሚችለውን ጠብቀው እንዲፅፉ ብናደርግ በቁጥጥር እያስማርናቸው ነው፡፡

ሐ.የክሎዝ (cloze) ምንባብ የሚባለው በአንድ ምንባብ ውስጥ ስድስት ወይም ሰባት ቃላት እየዘለሉ ክፍት ቦታ በመተው ተማሪዎች ከምንባብ ድባብ ተነስተው ክፍት ቦታዎችን እንዲያሟሉ ወይም አማራጮች ተስጥቷቸው ከአማራጮቹ እየመረጡ የሚያሟሉበት ክንውን ነው፡፡አሟልተው ሲገለብጡ የእጅ ፅህፈታቸው በዓላማ ሊያሻሻሉ ይችላል፡፡

መ.የቃላት ፅህፈት ክንውን ፡-አንድ ተማሪ ከመማሪያ መፃህፍት ከጋዘጣ፤ከመፅሔት ፤ከበራሪ ፅሑፍ ወዘተ ብጤውን ወይም የቡድን አባላትን እንዲያፅፉ በማድረግ ከዚያ በስርዓት ለመተራረምና በመጨረሻ ፅሑፉን እያዩ አስተካክው እንዲፅፉ ማበረታታት የመምህሩ ተግባር መመሪያ መስጠትና እየተከታተለ ማነቃቃት ይሆናል፡፡

ረ. የቅነሳ ክንውን፡-አንድ አረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ እንዲሁም ምንባብ አስፈለግ ያልሆኑ ቃላት አስወጥተው የተሰተካከለውን ሃሳብ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ተማሪዎች ማዘዝ ፤የቃላትና የሰዋሰው እወቀት ከማግኘታቸው በላይ የጽህፈትን የእምነት ባህሪሊለማመዱ ይችላሉ፡፡

## 2.5.2 የምሪት ፅህፈት ትምህርት ክንውን

ይህንን የጽህፈት አይነት ከቁጥጥር ጽህፈት በተሻለ ለተማሪዎች ዉስን ነጻነት የሚሰጥ ሲሆን ለተማሪዎች የተወሰነ ምሳለ በመስጠት ምሳለዉን ተከትለዉ እንዲጽፉ እድል የሚሰጥ ነዉ፡፡ለምሪት ጽሁፍ መነሻ የሚሆኑ ለሎች የጽሁፍ ስራዎችና የእይታ ምንባቦች ሊቀርቡ ይችላሉ ፡፡የሚከተሉን ክንዉኖች በዉስጡ ያካትታል፡፡

**1.ማጠቃለያ የመስጠት ክንዉን**

አንድ የጽሁፍ ምንባብ አንብበንላቸዉ ወይም ራሳቸዉ አንብበዉ የተረዱትን ጠቅለል አድሪገዉ በራሳቸዉ አባባል እንዲያቀርቡ መጠየቅ ፍረነገሩንና የሀሳብ ቅደም ተከተል እንዲጠበቅ ሳለ ቃላት አመራረጥ የአረፍተ ነገር አሰካክና የስርአተ ነጥብ ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ ነዉ፡፡

**2. ማስታዎሻ የመያዝ ክንዉን**

ከቋንቋ ትሚህርት ዉጭ በለሎች ትምህርት በመምህራቸዉ ገለጻ ሲደረግላቸዉ ማስታዎሻ ይዘዉ ለቋንቋ መምህር እንዲያሳዩ ማድረግ ወይም በያዙት የጽሁፍ ማስታዎሻ ላይ ከብጠዎቻቸዉና ከብዱን ኣባላት ጋር የጽህፈትን ባህሪ ጠብቀዉ ስለመጻፋቸዉ እንዲያወያዩ ማድረግ የዉይይታቸዉ መጨረሻ የጋራ ማስታወሻ እንዲያዘጋጁ ማሰራት፡፡

3.ጅምር ሀሳብ የማስጨረስ ተግባር

ጅምሩን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ከራሳቸዉ ሀሳብ ኣፍልቀዉ እንድጨርሱ መጠየቅ ኣላማችን ጅምሩን ሲጨርሱ የጽህፈት ስርአት ጠብቀዉ መጻፋቸዉን ለማየትና ጥሩ ከሰሩ ለማበረታታት ችግር ካለባቸዉ ለማስተካከል ነዉ፡፡

4.የእለት እለት መዝገብ ተማሪዎች በእለት እለት ያጋጠማቸዉን ዋና ዋና ነገር መዝግበዉ እንዲይዙና የወሩን ለክፍል ጋደኞቻቸዉ እንድያቀርቡ ቢደረግ ጥሩ የጽህፈት ልምድ እንድያዳብሩ ልንረደቸዉ እንችላለን፡፡

### 2.5.3 ካርታዎች ፣ግራፎች፤የስታስቲካዊ ዳታዎችን በጽሁፍ ተንትኖ የማቅረብ ክንዉን

ይህ ክንዉን ከካሪታዎች ፣ከግራፎችና ከዳታዎች የተለያዩ መረጃዎችን በመረዳት በጽሁፍ እንድያቀርቡ በጋራ የተስማሙበት አቀነጅተዉ እንድጽፉ በማድረግ የጽህፈት ክህል እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡

### 2.5.4 መልሶ ምገባ መስጠት (Feedback)

የመልሶ ምገባ መሰረታዊ አላማ ተማሪዉ የተለያዩ ክንዉኖችን ስያከናዉን እንደታሰበዉ ባከናወኑት ክንዉን በኩል የአስተሳሰብና የአሰራር ለዉጥ ለማምጣት ከሆነ መበረታታትና መነቃቃት እንዲችል የሳተዉና ያላወቀዉ ካለ እንዲያዉቀዉና ማስተካከያ እንዲያደርግ ነዉ፡፡ይህን ማድረግ ደግሞ ቀላል ስራ አይደለም በማለት (እነ አቶ ሰለሙን 1994) Devid kross በመጥቀስ ያብራራሉ፡፡

እንደዳንአል (1998፣76) አገላለጽ ተማሪዎች በጽህፈት ለዉጥ እንዲያመጡ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡የተለያዩ መልመጃዎች እንዲሰሩዋቸዉ ይገባል፡፡መልመጃዎች የሚመረጡት በደረጃቸዉ በመከፋፈል ሲቀሪብ የበለጠ ይሆናል ፡፡የጽህፈት መልመጃዎች በሶስት መድቦ ማየት ተገቢ እንደሆነ በመጥቀስ ዳንአል የገልጸዋል ፡፡ስለዚህ እንደ ዳንአል አገላለጽ የጽህፈት መልመጃዎች ደረጃ የሚባሉት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሀ. የቁጥጥር ጽህፈት፡-ተማሪዎች ሀሳባቸዉን በነጻነት ማፍለቅና ግለ ቋንቋ የመጠቀም እድል የሚሰጥ የጽህፈት መልመጃ አይደለም፡፡በጽህፈት ሂደት ዉስጥ የሚያስፈልጋቸዉ በሙሉ በመምህራቸዉ ይሰጣል፡፡

ለ. የምሪት ጽህፈት፡- Devid Cross (1991:274) ስለምሪት ጽህፈት ሲገለጽ የምሪት ጽህፈት መልመጃ መሰረት የሚያደርግ ናሙና ጽሁፍ ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ተመሳሳይ የጽሁፍ ስራ እንድሰሩ ማድረግ ነዉ፡፡

ሐ.ነጻ ጽህፈት ፡-ይህ መልመጃ በፊደላት ቅሪጽ፣ስለ ቃላት አመራረጥ ፣ስለ አረፍተ ነገርና አንቀጾች ባህር ፣ስለ ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ያላቸዉ እዉቀትና ልምድ በመጠቀም በመረጡት ርእስ ለፈለጉት የአደራረስ አይነት ፣በፈለጉት መጠን የሚጽፉበት ሁነታ ያስያል፡፡(እነ ሰለሙን፣1994፣144)

## 2.6. የጽህፈት ክህልን ለማዳበር የሚረዱ መልመጃዎች አዘገጃጀትና አደረጃጀት

የጽህፌት ክሂል መልመጃዎች ተማሪዎችን የሚያግባቡ ወይም መልእክት ያለዉን ጽሁፍ እነድያዘጋጁ የሚያበረታቱ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡የጽህፈት መልመጃ አዘገጃጀት አስመልክቶ ቅድስት ማርያም ዩኒቨረስቲ ኮሌጅ (2008፣88) ባዘጋጀዉ አማርኛ የማስተማር ስነ.ዘደ መጽሀፍ እንደሚከተለዉ ያስቀምጣል

ሀ.የሚዘጋጁት የጽህፈት ክህል መልመጃዎች በቡድን ሆነዉ በዉይይት የሚሰሩ ቢሆኑ የተሻለ ነዉ፡፡

ለ.የሚዘጋጁ የጽህፈት ክህል መልመጃዎች የተማሪዎቹ ፍላጎት ስመት የቀረቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሐ.የሚዘጋጁ የጽህፈት ክህል መልመጃዎች ተመጣጥነዉ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

መ.የሚዘጋጁ የጽህፈት ከህል መልመጃዎች በጣም ረጅምና አሰልች መሆን የለባቸዉም፡፡

### 2.7. ሥነ-ልቦናዊ እና አእምሯዊ ባህሪያት

በጽህፈት ትምህርት ላይ ተጽእኖ ከሚያሰድሩት ተለውጦዎች መካከል ሰነ ልቦናዊ፤ሰነ ልሳናዊና ሰነ አእምሯዊ ሁኔታዊች እንደሆኑ Byme (1991)፤Richards(1990) እና Norrish (1983)

በመሆኑም ቀጥለን የተወሰኑትን በዝርዝር እንመልከት

ሀ.ስነ ልቦናዊ ባህሪ -ጽህፈትን የማፍለቅ ተግባር የሚያከናወንበት ክህል እንደ መሆኑ መጠን አንባብን እያሰቡ መጻፍ የማይቀር ነዉ፡፡ጸሀፊዉም መልእክቱን ለአንባቢ ግልጽና ሳቢ በሆነ

መንገድ ለማድረስ ሲል ከወዲሁ በሀሳብና በጭንቀት የሚሞላበት ሁነታ ይኖራል፡፡ይህም የጽህፈት ክህልን አስቸጋሪ ተግባር ያደርገዋል፡፡በንግግር ጊዜ ግን ተናጋሪዉ ወዲያዉ ከአድማጭ ምጋበ ምላሽ የዘገየ ነዉ

ለ.ስነ አእምሮአዊ ባህሪ-ጽህፈት በልምድ ሳይሆን በትምህርት ሂደት የሚገኝና የአእምሮን ዉሰጣዊና ረቂቅ ተግባርን የሚጠይቅ ዉስብስብ ክህል ነዉ፡፡ጽህፈት እንደደረጃችን ፈተናን ለማለፍ አልያም ለክህልነቱ ብቻ የምንማረዉ ጥበብ አይደለም፡፡ይልቁንም ትምህርቱ ለሎች ክህሎችን ለመማርና ተጨማሪ እዉቀቶችን ለመቅሰሚያነት ያገለግላል፡፡ጽህፈት ሀሳብን ከኣእምሮ አመንጭቶ በወረቀት ላይ አስተካክሎ ማስፈር ከባድና አእምሮን ሊፈትን ይችላል፡፡

2.8. የጽህፈት ክህል አቀራረቦች

የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች በሁለት እንደምመደቡ የተለያዩ ምሁራን ያመለክታሉ፡፡እነዚህም ዉጠት ተኮር አቀራረብና ሂደታዊ አቀራረብ እንደሆኑ

- **ዉጤት ተኮር አቀራረብ**

ዉጤት ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ ትኩረቱ ከጽህፈት ሂደት ይልቅ ተማሪዎች በምያፈልቁት የመጨረሻ ዉጤት ላይ ነዉ፡፡

በዉጠት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ጽህፈትን ሲማሩ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት

ሀ.የትዉዉቅ ደረጃ፡-ተማሪዎች ወደ ዋናዉ የጽህፈት ስራ ከመግባታቸዉ በፊት በመምህራቸዉ የሚቀርብላቸዉን ሞደል ጽሁፍ በማንበብ ለመጻፍ ራሳቸዉን የሚያዘጋጁበትና ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ የሚያደርግ ደረጃ ነዉ፡፡

ለ.የልምድ ደረጃ፡-የልምድ ደረጃ ተማሪዎች የተለያዩ ጽሁፎች ጋር ከተዋወቁ በኋላ በራሳቸዉ ተነሳሽነት የራሳቸዉን ሀሳብ እያፈለቁ መጻፍን እንዲለማመዱ የሚያደርግበት ደረጃ ነዉ፡፡

ሀ.የዉጤት ደረጃ፡-በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ከላይ ባሉት ደረጃዎች የተለማመዷቸዉን የጽህፈት ስራዎች ወደ ዉጤት የሚቀይሩበት ደረጃ ነዉ፡፡

- **ቅድመ ጽህፈት** (Free writing)

ጸሀፊዎች ሀሳብን የሚያስባስቡበት አንባቢያንን የሚያስቡበት አበይት ነጥቦችን የሚያቀርቡበት፤ጊዚያዊ እቅዳቸዉን የሚነድፉበትና በአጠቃላይ ወደ ዋናዉ የጽህፈት ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ሂደት ነዉ፡፡

- **የጽህፈት ጊዘ** (white writing)

ሁለተኛዉ የጽህፈት ደርጃ በቅድመ ጽህፈት የተመረጠን ሀሳብ መልክ በማስያዝ በወረቀት የሚያሰፍርበት ነዉ፡፡

- ድህረ ጽህፈት (Post-writing)

በዚህ ደረጃ ጠቅላላ የክለሳ ንባብ የሚደረግበት በመሆኑ ተደራስያን ያለምንም ችግር ጽሁፉን አንብበዉ ሀሳብን እዳያገኙ ለማድረግ የሚስተካከል ነገር ካለ የምናስተካክልበት ደረጃ ነዉ፡፡

## 2.9 የጽህፈት ክህል መልመጃ አይነቶች

ጽህፈትን የማስተማር ሂደት የጽህፈት ክህል መልመጃዎች ተማሪዎችን የሚያግባቡ ወይም መልእክት ያለዉ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ የሚያበረታቱ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ስለሆነም የፅሁፍ ክሂል መልመጃዎች ሲዘጋጁ የሚከተሉት ነጥቦች ላይ በናተኩር የተሸለ እንደሚሆን Pincas (1989:2) ይናገራሉ፡፡

1.ፅህፈት ክሂል መልመጃዎች ተግባራዊና ጠቃሚ በሆኑ የፅፍት አይነቶች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል፡፡

2. የፅፈት ክሂል መልመጃዎች የሚያተኩሩበት ልምምድ ተግባቦታዊ ወይም አገልግሎታዊ መሆን አለባቸው፡፡

3. የፅፈት ክሂል መልመጃዎች ሰዋሰውና ቃላት ለማስተማር ከመርዳታቸው ጎን ሌሎች ክሂሎችንም ለማሳደግ የሚረዱ መሆን አለባቸው፡፡

## 2.10 የወጤታዊ አቀራረብ የጽህፈት ደረጃዎች

በውጤታዊ አቀራረብ ፅህፈትን በማስተማር ሂደት በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናል፡፡እነዚህም ተግባራት ውስን ፅህፈት፣ምርምር ፅህፈትና ነፃ ጽህፈት ደረጃዎች ናቸው፡፡ Pincas (1982:14) ፣Rams (1983) እና Richards (1990:107)::

ሀ.ውስን ፅህፈት (controlled writing)

ለ.ምር ፅህፈት (Guided writing)

ሐ.ነፃ (ልቅ) ፅህፈት (Free writing)

- **በውጤታማ አቀራረብ የፅፈት ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና**

በውጤታዊ አቀራረብ ማስተማሪያ ዘዴ የመምህሩ ሚና በአብዘኛው የቋንቋውን ሰዋሰውን ህጎች ማስተማር፣ የተማሪዎችን የመጨረሻ ውጤት ሰብስቦ ሰዋሰዋዊ ስህተቶችንና የአጻጻፍ ሥርዓተ ግድፈቶችን ማረም የፅሁፉን ጥሩነትና መጠፎነት ከትክክለኛነት አንጻር መገምገም ፣ለመማር የሚበረታታ አስተያየት ወይም ውጤት መስጠት ነው፡፡ በውጤታዊ አቀራረብ ፅህፈት ለማስተማር የሚዘጋጅ መምህር ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ተገቢውን ዝግጅት ሊያደርጉ እንደምገባ BaYrne (1982:16) pincass (1988) Atkines እና ሌሎች (1995)፡፡

- **በሂደታዊ አቀራረብ የፅህፈት ማስተማር ዘዴ የመመህሩ ሚና**

በሂደታዊ አቀራረብ ፅህፈትን የሚያስተምር መምህር የተማሪዎች የእርስ በርስ መማማር ወይም ተራክቦ ቦታውን እንደምለቅ ጠናትች ይተቁማሉ፡፡ በዚህ መሰርት መምህሩ መማርን የማመቻቸትና የመከታተል የተማሪዎችን የጽህፈት ተግባቦታዊ ክሂሎች የማዳበር የተማሪዎችን ፅሁፍ የማንበብ ፣የመገምገምና የማማር እንዲማሩ የማገዝ መማርን የማፋጠን Rudder(1999) Scrivener(1994) እና Hedge (1999:7) እና Leki(1994:57) ሚና ይጫዎታሉ፡፡ በአፃፃፍ ሂደትም ተማሪዎች በማሰለሰል ፣በማቀድ፣በማረርቀቂ በመከለስ ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ያደርጋል፡፡

- **በሂደታዊ አቀራረብ የፅህፈት ትምህርት የተማሪው ሚና**

በትምህርት ሂደት ተማሪው ሚና መማር ነው፡፡ መማር ማከናውን ያለበትም የነገሩትን በማዳመጥና የሰጡትን በጭፍን ሳይሆን በመስራት ፣በመሞከርና በማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህም በተማሪው የመማር ሚና ላይ የሚከሰተው ልዩነት ለተማሪው ከሚሰተው ትኩረት የሚመነጭ ሲሆን ፣በመማሩ ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እንዲያሳድር መገመት ይቻልል፡፡የተማሪው ሚና ለመማር የሚያበረክተው አስተዋፆኦ በማስተማር አቀራረቦችና ስነዘዴዎች ውስጥ በግልፅም ሆነ በውስጠታዋቂነት ይታያይ፡፡ይህም በትምህርቱ በሚቀርብው ይዘት ላይ በሚኖረው ተነሳሽነት እና በሚሰራበት ቡድን ውስጥ ባለው ተሳትፎ ሊገልፅ ይችላል፡፡(Richards and Rodgers፣ 1986:23)

## 2.11 የፅህፈት ክሂልን መመዘን

የፅህፈት ክሂል ለመመዘንና ለመገምገም ስናስብ Pinkas (1989:32) በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማትኮር እንደሚገባ ያሳስባል፡፡

1.የመግባባት ብቃት

2.በተጠይቃዊ አደረጃጀት

3. በቅርፅበአቀራረቡ

4. በሰዋሰው ቅንብር ደረጃው

5.በእጅ ፅሁፍ ፣በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና በመሳሰሉት መስፈርቶች የፅህፈት ክሂል ሊመዘንና ሊገመገም ይቻላል፡፡

## 2.12 ክሂል መልመጃዎች የአቀራረብ ቅደም ተከተል፡፡

የፅህፈት ክሂል መልመጃዎች ሲአጋጁ የሚከተሉት ሶስት ደረጃዎች መሰረት ቢያደርጉ የተሸለ ነው በማለት Pincas (1989, 78) በማለት ሃሳቡን ያቀርባል፡፡

1. የትውውቅ ደረጃ ፡- ይህ ደረጃ ከሚፅፉት የፅሁፍ ዓይነት ቅርፅና የይዙት አደረጃጀት ጋር የሚተዋውቁበት ደረጃ ነው፡፡ በጥንቃቄ የተመረጡ ምንባቦች በዚህ ደረጃ ውስጥ ጥሩ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

2. የልምምድ ደረጃ ፡-ይህ ደረጃ ከቀረበው የፅሁፍ ዓይነት ቅርፅና የይዘት አደረጃጀት ጋር በበቂ ሁኔታ መቻላቸውን የምናረገግጥበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ስር የሚቀርቡት መልመጃዎች ውስን ናቸው፡፡ መልመጃዎች ከአንድ ፅሁፍ ላይ የሚጎድለውን ነገር የመሙላት አደረጃጀት የማስተካከልና የመሳሰሉት የሚጠይቁ ሊሆን ይችላል፡፡

3.የውጤት ደረጃ ፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ የጎደለውን ነገር ከሞምላትና አደረጃጀትን ከማስተካከል አልፈው ከራሳቸው በመፍለቅ ወጥ የሆነ ፅሁፍ ያዘጋጃሉ፡፡ ለምሳሌ በትውውቅ ደረጃ ከደብዳቤ አፃፃፍ ጋር ተዋውቀው በተከታይ ደረጃ ዳግም ስለ ደብዳቤ ቅርፅና የይዘት አደረጃጃት ከተለማመዱ ፣በዚህ ደረጃ ደግሞ ሊፈለጉት ዓላማ ሊውል የሚችል የተሟላ ደብዳቤ ስርዓቱን በመጠበቅ ከራሳቸው አፍልቀው ይፅፋሉ፡፡

## 2.13 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

በአማርኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በፅህፈት ከሂል ስለሚፈፅሟቸው ስህተቶች ላይ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከጥናቶች መካከልም አብዘኞቹ ለ2ኛ ዲግሪማሟያነት የቀረቡ ናቸው፡፡

ሰይድ (1993) በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሀፍት የቀረቡትን የፅህፈት ትምህርት ይዘቶችንና ክንውኖችን የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ በሚል ርዕስ የማስተር ኤም ኤ ዲግሪ ባቀረቡት ጥናት ተማሪዎች በፅህፈት ትምህርት ጊዜ ፅህፈትን በተግባር እየተለማመዱ እንዳይማሩና የብጠ እሪማትን ተግባራዊ እንዳማይሆን የገለጹ ስሆን በጥናታቸው ውጤት ማጠቃላያ ላይ የፅህፈት ትምህርት ተግባር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

በመሆኑ የተመራማሪው ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የፅህፍት  ትምህርትአተገባበር ላይ ያተኮረ ስሆን የዚህ ጥናት ግን የሚተኮረው የፅህፈት ችሎታ በንፅፅር በተግባር በመፈተሽ ችግሮችን ለይቶ የመፍተሄ ሀሳብ ማቅርብ ላይ ነው፡፡ እንደሁም በጊዜ እና በቦታ ስለማይገናኝ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው የለም፡፡

ሰለሞን (1991፡7) Zamel (1992)ን በመጥቀስ መጻፍ ሂደታዊ ከመሆኑ ባሻገር ዓላማ ያለው ( Purposeful) እያደረገ የሚሄድ  (Evolutionary) ድግግሞሽ ወይም ተመላላሽነት ያለው (Recursive)  ምልልምስ  (Dialogic) ፊሳሴ ( Fulid) ) እና አሳሽ (Explatory) እንደሆነ ገልጽዋ ፡፡

ይህ አገላለጽ ሰው በጽህፈት በኩል ይማራል ፣ያስባል ፣እውቀትንም ገንዘቡ ማድረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪ ጽህፈት አዲስ ሃሳብን የማመነጨት ዘዴ በመሆን ሀሳብን በሚታይና ቋሚ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላለፍ ምሁራን እውቀታቸውን እንዲያንጸባርቁበት በማህበራዊ ህይወትም ውስጥ ማስታዎሻ ለመያዝ ደብዳቤ ለመጻፍና ሪፖርቶችን ለማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ትኩረት ይሚያደርገው አፋቸውን በወላይተኛ ቋንቋ የፈቱ የግል ና የመንግስት ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ሲህተት ንጽጽር ነው፡፡ በዚህ መሰረት አጥኝዋ መረጃውን ሰብሰባ ያጠናቀቀችው ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት መጠናዊ ምርምር እና በደጋፊነት ዓይነታዊ ምርምር ሥራ ላይ ውለዋል፡፡

በዚህ አጥኝዋ ቅይጥ ምርምር የተጠቀመችበት ምክንያት ምርምሩ የሚተነተነው በቁጥር መረጃ ትንተናና በገለጻ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኚዋም በቁጥር ለምገለጸው የመረጃ ትንተና አመች ሆኖ ስለገኘችው ልትመርጠው ችላለች፡፡ሌላው በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት በቁጥር መረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በገለጻ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ስለዚህ በቁጥር ከሚተነተነው ውጭ ይህ መረጃ አይነታዊ ምርምር ዘዴ የተከተለ ሰሆን አቀረራቡ ግን በገላጭ ንድፍ ላይ የተመሰረ ነው፡፡

## 3.2 የናሙና ዘዴ

### 3.2.1 የጥናቱ አካባቢ ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ተተኳሪ የሚሆነዉ በወላይታ ዞን አረካ ከተማ አስተዳደር ነዉ፡፡ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ ስለምትኖርበትና ስራዋንም በዚሁ አካባቢ የምትሰራ ስለሆነ ለጥናቱም በቂ የሆነ መረጃ ለማግኘት የተሻለ ስለሚሆን ነዉ፡፡

### 3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በአረካ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ሁለት ትምህርት ቤቶችን፣አረካ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ዱቦ እመቤታችን ቅድስት ማርያም ካቶሊክ ትምህርት ቤት ሲሆን የተመረጡት በአመቺ ናሙና ዘዴን በመጠቀም ነዉ፡፡

ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡበት ምክንያት አጥኝዋ የምትሰራበት ትምህርት ቤት እና የምትኖርበት አካባቢም በመሆኑ በማንኛዉም ሰኣት ጥናቱን ለማከናወን ከቦታ አኳያ ቅርበት ያለዉ ፣መረጃዉን ለመሰብሰብ አመችነት ያለዉ በመሆኑ፣እንዲሁም ሌላ የግል ትምህርት ቤት ያለመኖሩ ሌላዉ ምክንያት ነዉ።

## 3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በአረካ ከተማ አስተዳደር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ዉስጥ የዘጠነኛ ክፍል ብቻ ተተኳሪ የሚያደርግ ሲሆን የተመረጡበት ምክንያት አጥኚዋ በዚሁ የክፍል ደረጃ በማስተማር ላይ የምትገኝ ስለሆነች በጽህፈት ከሂል ትምህርት ላይ ችግሩ ጎልቶ ሰላየችዉ ነዉ።

### 3.2.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ሲመረጡ በቅድሚያ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች በወላይተኛ ቋንቋ አፍ የፈቱ ተማሪዎች የመለየት ስራ ተሰርትዋል።እነዚህ ተማሪዎች ከታወቁና ከተለዩ በኂላ ለጥናቱ አስፈላግጊ የሆኑ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 65 ተማሪዎች በድምሩ 130 ተማሪዎች ተመርጠዋል። ይህ የሚሆነዉ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ያሉት በወላይተኛ ቋንቋ  አፍ የፈቱ ተማሪዎች ድምር ለተጠኝ ተማሪዎች ቁጥር በማካፈል ተሰረትወል፤ በሚገኘው ውጤት አንጻር ከተተኳሪ ተማሪዎች የስም ዝርዝር በተወሰነ ረድፍ ርቀት ላይ የሚገኙት ስሞች በመውሰድ ተለይተዋል። በዚህ መሰረት በዱቦ የእመቤታችን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላላ በወላይተኛ አፍ የፈቱ ተማሪዎች ብዛት 240 ሲሆን የሚፈለገው ተማሪዎች ብዛት 65 ብቻ ነዉ።ስለዚህ 240÷65=3.69 ። እንደዚሁም የአረካ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጠቅላላ 224 ናቸው።  224÷65=3.44 ነዉ።በዚህ ውጤት መሰረት ከስም ዝርዝራቸው በየሶስት ተማሪዎች ርቀት ተማሪዎች ተመርጠዋል።

## 3.2.5 የመምህራን የናሙና አመራረጥ

በጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ነበር ።በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ያሉት ከ9ኛ እስከ 12ኛ የሚያስተመሩ መምህራን

በቁጥር 4 ሲሆኑ ሁሉም ሁሉም ተካትተዋል ፡፡ስለዚህ አጠቃላይ ናሙና ዘዴን በመጠቀም በጥናቱ እንዲካተቱ ተደረጋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱን ለማካሄድ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ተማሪዎችን አንቀጽ በማጻፍ መፈተን ዋና የመረጃ መሰብሰብያ ሲሆን ፣የጽሁፍ መጠይቅ ፣እና የመምህራን ቃል መጠይቅ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ጥቅም ላይ ዉለዋል፡፡

### 3.3.1 ለተማሪዎች እንዲጽፉ የተሰጠ ድርሰት

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማደራጀት እና ለመተንተን በቅድሚያ ለጥናቱ የተመረጡ 130 ተማሪዎች አንቀጽ/ድርሰት እንድጽፉ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ አንቀጽ/ድርሰት ለመጻፍ በሁለት የአማርኛ መምህራን የተገመገሙ፤የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ፣ባህል እና የአኗኗር ዘይቤ መሰረት ያደረጉ ሰባት ርዕሶች ቀርበዋል፡፡

ተማሪዎቹ ከቀረቡት ርዕሶች ውስጥ ሁለት ሁለት ርዕስ መርጠው በአንዱ ርዕስ ክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ሲደረግ፣በሁለተኛው ደግሞ ቤታቸው እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በተማሪዎቹ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙት ስህተቶች ከእዉቀት ማነስ ብቻ የመጡ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ ጊዜ ወስደው በሚጽፉት ጽሁፍ ለመለየት ስለተፈለገ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል ድርሰቶቹ በአራት ቅጅ ተባዝተው በአራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታርመዋል፡፡

የአስተራረም ሂደቱ አራሚዎቹ በአንቀጾቹ ውስጥ ሊያገኟቸው የሚችሉትን ስህተቶች በተዘጋጁ የቅድመ ምደባ መስፈርቶች እንዲመድቧቸው ተደርገዋል፡፡እነዚህ የምደባ መስፈርቶች የተዘጋጁት አጥኚዋ አስቀድማ ድርሰቶችን በማረም ካገኘችው ስህተቶች መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ለስህተቶቹ የተዘጋጁት ምድቦች የሆሂያት (የፊደላት) ቅርጽ ግድፈት፣የቃላት ስህተት ፣የሥርዓተ ነጥብ ስህተት፣የዐረፍተ ነገር አገባብ ስህተት እና የቋንቋ አጠቃቀም ናቸው፡፡በዚህ መለኪያ መሰረት መምህራኑ ያገኟቸውን ስህተቶች ብዛት እንዲመድባቸው ተደርጓል፡፡በዚህ መንገድ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ታርመው የተከፋፈሉትን ስህተቶችን ለማመሳከር በአራቱም አራሚዎች እርማት የተገኙ የጋራ የሆኑት ተወስደው ለጥናቱ በሚመች መልኩ ተደራጅተው

ተተንትነዋል፡፡ስህተቶችን በአይነት በአይነት ለመመደብ ስህተቶቹንም ለመቁጠር እና ስህተት ትንተና ለማድረግ የሚጠቅሙ ሁለት አበይት ዘዴዎች አሉ፡፡

እነሱም ቅድመ ግንዛቤ መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ዘዴ እና ስህተትን መሰረት ያደረገ የአከፋፈል ዘዴ ናቸው (Narrish,1983 81-89) ፡፡ከነዚህ ዘድዎች ውስጥ በዚህ ጥናት አገለግሎት ላይ የዋለው ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ባደረገ ምድብ ውስጥ የተማሪዎችን ስህተቶች መመደብ ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በመጠኑም ብሆን አሻም የሆነውን የአከፋፈል ዘዴ የሚያቃልል እና ለአከፋፈል የሚያመች በመሆኑ ነው፡፡

## 3.3.2 የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ

ይህ የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ በአጥኚዋ ተዘጋጅቶ በአማካሪዋ አስተያየት ተሰጥቶበት የተዘጋጀ ሲሆን ሁለት ክፍሎችን ይዟል፡፡ እነርሱም ክፍል አንድ የሊከርት ስከል መሰረት አድርገው አንድ አስር ጥያቄዎችን የያዘ ዝግ እና ሁለት በጽሁፍ የሚመለሱ ነፃ ጥያቀዎችን የያዘ ነው፡፡ ተማሪዎቹ መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት ስለ አሞላሉ በአጥኚዋ በቂ የሆነ ገለጻ የተደረገላቸው ሲሆን በሚሞላበት ሰዓት የእያንዳንዳቸውን የተመለከተች መሆኗን ይገልጻል ፡፡

## 3.3.3 የመምህራን ቃል መጠይቅ

በአራቱ ተተኳሪ መምህራን ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ የሚገኘው ምላሽ በተማሪዎች የአንቀጽ ጽህፈት ወቅት ለስህተት መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ መረጃዎች እንደሚያስገኝ ታምኗል፡፡ መጠይቆቹ በዘጠነኛ ክፍል አማርኛን በሚያስተምሩ መምህራን ብቻ ተመልሷል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

አጥኚዋ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተሰበሰበውን መረጃ ዓይነታዊ እና መጠናዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ በመከተል ተንትኗል፡፡ አሃዛዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በጽሁፍ መጠይቅ ወቅት በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መሀከለኛ፣ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ በመባል የሚሰበሰቡ መረጃዎች በሰንጠረዥ ውስጥ በአሃዝ ማለትም በቁጥርና በመቶኛ ስለሚገለጹ ሲሆን፤ ዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ ደግሞ በአሃዝ የተገለጹት መረጃዎች ተተንትነውና ተብራርተው የጥናቱ ውጤት የሚቀርበው የገለፃ ስልትን ተከትሎ በመሆኑ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና የዉጤት ማብራርያ

በዚህ ምዕራፍ በናሙና ከተመረጡ ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን በምዕራፍ አንድ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በዚህ መሠረት የግል ትምህርት እና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የፃፏቸው አንቀጾች በምዕራፍ ሁለት Narrish (1983)ን በመጥቀስ የቀረበውን የመጻፍ ስህተት መመዘኛ ነጥቦችን መሠረት በማድረግ የተሰበሰበው የተጠኚ ተማሪዎች እና የአራሚ መምህራን ዳራ፤የተማሪ ፈተናዎችና የጽሐፍ መጠይቅ እና የመምህራን ቃል መጠይቅ መረጃዎች ትንተናዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 4.1 የተጠኚዎች ዳራ

**ሠንጠረዥ 1፡- የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ**

| የት/ቤት ዓይነት | የተመረጠው ናሙና ብዛት | ፆታ | | | ዕድሜ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | 14 | 14-15 | 15-16 |
| ከመንግስት ት/ቤት | 65 | 37 | 28 | 65 | 13 | 42 | 10 |
| ከግል ት/ቤት | 65 | 39 | 26 | 65 | 16 | 40 | 9 |
| ድምር | 130 | 76 | 54 | 130 | 29 | 82 | 19 |

ከላይ በሠንጠረዥ አንድ የቀረበው መረጃ በአረካ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙ አንድ የግል እና የመንግስት ትምህርት ቤት አንድ የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሰጡ የተመረጡ ተጠኚ ተማሪዎች የጾታና ዕድሜ ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩት በወላይትኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በድምሩ 130 ሲሆኑ ወንዶቹ 76 ሴቶቹ ደግሞ 54 ናቸው፡፡

ከነዚህ መካከል 29 ተማሪዎች ዕድሚያቸው 14 አመት ሲሆኑ 82 የሚሆኑቱ ዕድሜያቸው ከ14-15 አመት ክልል ሲነኙ ደግሞ ከ15-16 አመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ይነኛሉ፡፡ ይህ

ሠንጠረዥ በዕድሜና ፆታ ተከፋፍሎ መቀመጡ የሚያሳየው የተማሪዎችን ቁልጭ ያለ ዳራ ለማሳውቅና በዕድሜ ምን ያህሉ በተቀራረቡ የዕድሜ ክልል እንደሚገኝና በፆታም በእኩል ደረጃ ላይ እንዳሉ ያረጋግጣል፡፡

ሠንጠዥ 2፡- ተማሪዎችን አንቀጾች የሚያሪሙ መምራን መረጃ

| ተ.ቁ | የመምራን የትምህርት ደረጃ | የተመረቁበት ትምህርት ዘርፍ | የአገለግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|
| 1 | የመጀመሪያ ዲድሪ | አማርኛ ትምህርት ክፍል | 15 አመት |
| 2 | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ ትምህርት ክፍል | 19 አመት |
| 3 | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ ትምህርት ክፍል | 16 አመት |
| 4 | ሁለተኛ ዲግሪ | አማርኛ ትምህርት ክፍል | 20 አመት |

ከላይ በሠንጠረዥ የቀረበው መረጃ በአረካ ከተማ አስተዳደር ሥር በዱቦ የእመቤታችን ቅድስት ማሪያም ካቶሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በአረካ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራን ዝርዝርና የትምህርት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በጠቅላላው አራት መምህራን ይገኛሉ፡፡እነዚህ መምህራን ተጠኚ ተማሪዎች የጻፉትን አንቀጾችን በማረም ለዚህ ጥናት የራሳቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡በመሆኑም አንዷ መምህር አማርኛ በማስተማር ስራ የመጀመሪያ ዲግር ያላት ሲሆን 15 አመት በማስተማር ስራ ያገለገለች ናት፡፡ሦስቱ መምህራን አማርኛ ትምህርት በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ አላቸው፡፡ አንደኛው 16 አመት በማስተማር ስራ ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛዋ 19 አመት በማስተማር ስራ ሲታገለግል ሦስተኛዋ ደግሞ 20 አመት በማስተማር ስራ ያገለገለች ናት፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የመምህራን የትምህርት ደረጃና ረጅም የሆነ የስራ ልምድ መኖር ለጥናቱ ተአማኝነት እንድኖረውና በቂ መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡

## 4.2 በተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጽ ትክክለኛ ሆሄ/ ፊደል/ ቅርጽ አጠቃቀም

የጹፍ ስራ እርማት መስጠት ሲታሰብ ግምት ውስጥ ማስገባት ያለብን ነገሮች የሆሄያት/የፊደላት/ ቅርጽና አወቃቀር ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ በታች ባሉት የመረጃ ሠንጠረዦች የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የጻፉቸው አንቀጾች በማረም

የተፃፉትን የሆሄያት ቅርጽ አጠቃቀም ግድፈቶችን በመቁጠር የተገኙ ስህተቶችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

## ሠንጠረዥ 3፡-የተጠኚዎች የሆሄያት ቅርጽ ግድፈት በተመለከተ ከአንቀጾቻቸውን የተገኘ ውጤት

| ስህተት | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | | | | | የመንግስት ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሆሂያት ቅርጽ | የአንቀጽ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የአንቀጾችብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተተት በመቶኛ |
| | 121 | 13320 | 110 | 36 | 0.297 | 0.27% | 121 | 13535 | 111.859 | 59 | 0.527 | 0.47% |

ቀደም ሲል እንደገለጸው በዚህንዑስ ክፍል በአንቀጾቹ ውስጥ የተገኙት ስህተቶች በሙሉ መረጃቸው በዝርዝር ቀርቧል፡፡ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው አንቀጽ መሰረት የአንቀጽ ብዛት እና ስህተት በመቶኛ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በሠንጠረዥ ሶስት መረጃ መሰረት ስህተቶቹ የተቆጠሩት ተጠኚ ተማሪዎቹ ሁለት ጊዜ በጻፏቸው 121 አንቀጾች ውስጥ ነው፡፡ አንቀጾቹ የተጻፉት ባአጠቃለይ በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች 13320 ሲሆኑ በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ 13535 ቃላት ነው፡፡ከዚህ ጋር ተያይዘው ከቀረበው ውጤት መረዳት እንደምቻለው የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ 36 የሆሄያት ቅርጽ  አጠቃቀም ስህተቶች ስቆጠሩ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ 59 ስህተቶች ተቆጥረዋል ፡፡

በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ በፍት የተሰራበት መንገድ ተግባራዊ በማድረግ ለመስላት ተሞክሯል፡፡በዚህም መሰረት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአንቀጾች ውስጥ የፈጸሙት አማካይ የሆሄያት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን አንቀጽ ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠን ለማወቅ ተችለዋል፡፡

በዚህ መሰረት 36 ÷121 =0.30 አካይ ስህተት ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስናገኝ ተማሪዎቹ አንቀጽ የጻፏቸው አማከይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው 111 መሆኑ ይታወሳል።

በመቀጠል የተፈጸመው ስተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደምከተለው ተሰልተዋል።

አማካይ ስህተት X100 =0.3 X100 = 0.27%

አማካይ ቃለተ 110

በሌላ በኩል በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፃፏቸው አንቀጾች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማውቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተስልቷል። በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፉት አንቀጽ ውስጥ 59 የሚሆኑ የሆሄያት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥሮ ተመዝግበዋል።የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለአንቀጹ ቁጥር በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህ መሰረት 59 ሲካፈል ለ121 እኩል ይሆናል 0.47 አማካይ ስህተት መሆን ተረጋግጧል።አንቀጽ የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለጸው110 ነው።

አማካይ *100 = 0.527*100=0.47%

አማካይ ቃላት 111.9

ከመረጃ ትንተና መረዳት እንሚቻለው የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የፈጸማቸው የፊደላት ቅርጽ ግድፈት በአማካይ 0.27 በመቶ ሲመዘገብ ፣የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የፈጸሙት የሆሄ ግድፈት ግን 0.471 በመቶ ነው። ይህ የሚያመለክተው ትክክለኛውን የሆሄ ቅርጽ በአንቀጾቻቸው ውስጥ በመጠቀም ረገድ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሸሉ ሆነው ተገኝተዋል።

ከላይ በሰንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው በግል ትምህርት ቤት ከጻፉ አንቀጾች ውስጥ በፊደላት ቅርጽ (በሆሄያት አጣጣል ) ብዙ ስህተት እንደተገኘ ለማውቅ ተችሏል።

በዚህ የስህተት ምድብ ውስጥ የታዩ ስህተቶች በአማርኛ የፊደል ገበታ ውስጥ ያለ ቅርጽ ቢሆኑም ፊደላቱ በአንቀጽቹ ውስጥ መገኘታቸው ሆሄያትን ተገቢን ባልሆነ ቦታ መጠቀም ነው።

እነዚህ ስህተቶች በአብዘኛዎቹ ተጠኚ ተማሪዎች ጽሐፍ ላይ የታዩ ችግሮች ናቸው፡፡ አብነት ያህል የሚከተለውን ማየት ተችሏል፡፡

"እድሜ ለትምህርት ከመድርሱ በፍት ከጎደኛዎች ጋር በሰፈሪ እንጫዎት ነበረ"

"ባመጣውአረፈ ውጤት"

"ጠንካራና ተፈካከር ለመሆን ትምህርተን አጠናሎ"

"መምህራን በጣም ነው ምወደው"

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ስህተቶች በሳስት ከፍሎ ለማየት ተሞክሯል፡፡ አንደኛው የሆሄያትን ቅርጽ ሙሉ በሙሉ በመቀየር የተከሰተ ስህተት፣ሁለተኛው አንዱን ሆሄ በሌላ በመተካት የፈጠረው ስህተት፣ሶስተኛው አይነት ስህተት ደግሞ ፊደላትን ከቃል ውስጥ በማስወገድ የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው፡፡

እነዚሁም ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፉ አንቀጾች የተገኙ የሆሄያት ስህተት ብዛት 59 ሲሆን አማካይ ስህተቱ 0.53 ተሰልቶ 0.47 ነው፡፡ በእነዚህ ተማሪዎች ከጻፉ አንቀጾች ውስጥ በፊደላት ቅርጽ ግድፈት የተፈጠሩ ስህተቶች ቀጥሎ እንደቀረቡ ናቸው፡፡

"---እኛም ባንቺኩራ---"

"-- ት/ቤቱ ለሞኖሪያ ቤታች በመረታዊ--"

"---ከተፈተንኩ በእላ--"

"---ተወለድኩ---" "---ከልጅነት---"

"---ተሚሬ ስራ ሲይዝ የተቸገሩት ማዳን ፈልጋለ ፈልጋለሁ---"

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ስህተቶችን በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከተፈጠሩት ስህተቶች በተመሳሳይ በሶስት መልክ ታይቷል፡፡ አንደኛው የሆሄያትን ቅርጽ ሙሉ በሙሉ በመቀየር የተከስተ ስህተት ፣በሁለተኛ አንዱን ሆሄ በሌላ በመተካት የተፈጠሩ ስህተት፣ሶስተኛው አይነት ስህተት ደግሞ ፊደላትን ከቃል ውስጥ በማስወግደ የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው፡፡ አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ የፊደላትን ትክክለኛ ቅርጽ አጠቃቀም በሚመለከት ከተተኳሪ ተማሪዎች የተገኘ የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽበሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ 4፡-ከተማሪዎች ጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የሆሄያት ቅርጽ ተኮር ምላሽ ትንተና

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምለሾች አመራጮች | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍሌ መምህር በጽህፈት ወቅት ስለምጠቀምባቸው የተለያዩ /ፊደላት/ቅርጽየሆሄያት አስተምረውኛል | በጣም ዝቅተኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| | | | 1 | 1.5 | 6 | 9.9 |
| | | ዝቅተኛ | 4 | 6.2 | 5 | 7.7 |
| | | መሀከለኛ | 22 | 33.8 | 21 | 32.3 |
| | | ከፍተኛ | 20 | 30.8 | 30 | 46.2 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 18 | 27.7 | 3 | 4.6 |
| 2 | በአማርኛ አንቀጽ በምጽፍበት ጊዜ ስለፊደላት ቅርጽ ጥንቃቄ አደረጋለሁ | በጣም ዝቅተኛ | 5 | 7.7 | 3 | 4.6 |
| | | ዝቅተኛ | 7 | 10.7 | 10 | 15.4 |
| | | መሀከለኛ | 10 | 15.4 | 18 | 27.7 |
| | | ከፍተኛ | 23 | 35.4 | 20 | 36.9 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 20 | 30.8 | 10 | 15.4 |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ አራት ጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ ከተሰጠው ምላሽ ለመረዳት እንደሚቻለው ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ 30.8% የሚሆኑት ድርሰትን በሚጽፉበት ወቅት ስለሚቀምባቸው የተለያዩ የሆሄያት/ፊደላት/ ቅርጽ መምህራኖቻቸው ስለማስተማራቸው መፍተኛ የሚል አማራጭ ሲወስዱ 46.2% የሚሆኑት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች መምህራኖቻቸውየሆሄያት ቅርጽ ስለማስተማራቸው ከፍተኛ የሚል አማራጭ ወስደዋል፡፡

በሌላ በኩል ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ 9.9% የሚሆኑት በጣም ዝቅተኛ ሲሉ 1.5% ያህሉ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ መምህራኖቻቸው የሆሄያት /የፊደላት/ ቅርጽ ስለማስተማራቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ይህንኑ ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ ለመምህራኑ የቀረበው ጥያቄ “ለክፍልዎ ተማሪዎች ስለአንቀጽ/ድረሰት/ አጻጻፍ ሲያስተምሩ ያግዟቸው ዘንድ ያደረጉዋቸው ድጋፎች ምን ምን ናቸው” የሚል ነበር፡፡ መምህራኑ ስመልሱ ብዙ ነገር እናግዛቸዋለን፡፡ ለምሳሌ፡- አንቀጽ ለመጻፍ የሀሳብ ፍሰት ፣የፊደላት ቅርጽ በአግባቡ መጠቀም

፣የቃላት አመራረጥ ሁኔታ ፣ የአረፍተ ነገር አሰካክ እና የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ወዘተ--- እናስተምራቸዋለን በማለት ተናግረዋልአ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ "ተማሪዎች አንቀጽ ወይም ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የሆሄ ቅርጽ ለመጠቀም የሚያደርጉት ጥንቃቄ ምን ያህል ነው" የሚል ሲሆን ፣መምህራኖች የሰጡት ምላሽ በጣም ጥቅቶች ጥንቃቄ በማድረግ ሲጽፉ በርካቶች ተማሪዎች ግን የፊደላት ግድፈት ይታይባቸዋል የሚል ነው።

በተጠኚ ተማሪዎች አንቀጾች ፍተሻና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሆሄያት ቅርጽ ያነሰ ግድፈት ታይቶባቸዋል። እነዚህ ተጠኚዎች በፊደላት ቅርጽ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ አሳየተዋል።

ይህም የCelece-Murcia,(1991) ሃሳብ የሚጋራ ነው። ተማሪዎች የፊደልን ቅርጽ በለየት ቃላትን መሥረታው የቃላትን ምርጫ እና አጠቃቀም በማውቅ ሀሳባቸውን በተገቢው ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ማስተላለፍ ይችላሉ ተብለዋል።

## 4.3. በተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጽ ተገቢ ቃላት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 5፡- የተጠኝዎች ቃላት አጠቃቀም በተመለከተ ከአንቀጾቻቸው የተገኘውን ውጤት

| ስህተት | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | | | | | የመንግስት ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የአንቀጽ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የአንቀጸ ችብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተተት በመቶኛ |
| | 121 | 13320 | 110 | 37 | 0.3 | 0.27% | 121 | 13535 | 111.9 | 46 | 0.38 | 0.34% |

ተገቢ ቃላት መጠቀም ሀሳብን ለመግለጽ ወይም ለማስተላለፍ መሰረታወ የተግባቦት ሂደት መሆኑ አይካድም፡፡በሠንጠረዥ ሶስት መመልከት እንደሚቻለው ከስህተት ምድቦች ውስጥ አንዱ የቃላት አጠቃቀም ስህተት እንድሆነ ተገልጿል፡፡ የቃላት አጠቃቀም ስህተት በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንቀጽ ውስጥ 37 ያህሉን ቁጥር የያዘ ነው፡፡የዚህ የስህተት ምድብ አማካይ መጠኑ ተሰልቶ 0.3 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ ደግሞ 0.27% ነው፡፡ ይህ ማለት የስህተት አይነቱ በአንድ አንቅጽ ውስጥ 0.27 ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል ማለት ነው፡፡

የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት*100 = 0.3*100=0.29%

አማካይ ቃላት 110

በሌላው በኩል በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፃፏቸው አንቀጾች ውስጥ የሚገኙውን የቃላት አጠጠቃቀም ስህተት 46 ነው፡፡ የዚህ ስህተት ምድብ አማካይ መጠኑ ተሰልተው 0.38 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ ደግሞ 0.34% ነው፡፡ ይህ ማለት የስህተት አይነት በአንድ አንቀጽ ውስጥ 0.34 ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል ማለት ነው፡፡

አማካይ ስህተት *100 = 0.38*100=0.34%

አማካይ ቃላት 111.9

ይህ የስህተት ምድብ በተጠኝ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጾች ውስጥ ከብዙ በጥቅቱ እንደምከተለው ቀርቧል፡፡

ምሳሌ፡-ከግል ትምህርት ቤት፡-

“---አርቅ አስብ ---“

“-----ሌሎችን የሚያከብር ወለጆችን የሚያከብር ለወሌጆቸችው የምታዘዝ--“

“---ስለኀበዝ ተማራ ተግባር---“

“---አንድ ጡሩ አላማ ያለው --ተራካብ ብሆን ---ያለሁን አሁን መጋገር---“

ምሳሌ፡- ከመንግስት ትምህርት ቤት፣

”---ኀበዙ ተማሪ ትምህርት ቤትከመምጣቱ ቦፍት ደፍተሩን መጻፉን ይንፌርሙን--“

“ ---ወተት ከእስሳት ---ለሰውነት ግንባታ አስፈታግ---መጠከር --“

“---ላልበና ---ሀጉራት---የፋስል ግንንምብ---ባእንዲሪሽን አባቶቻችን ያወረሰንን --“

“እናቴ እኔን ከማሪገዙም ቀን ጀምረው ስትካባከበኝ---“

“ ---ትልቅ አስዋፆ አበርከታይኛለች--- አይበቃ--- ስከፋይኝም---ቆሉ እየተመገባት--“
የመረጃዎች ትንተና እንደሚያሳየው የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ የቃላት አጠቃቀም አላቸው፡፡ ተቢውን ቃላት ለተገቢው ቦታ በመምረጥ የሚቀረብ የመጻፍ ሀሳብን በትክክል በማቀናጀት የመፃፍ ብቃት እንዲኖር ያደርጋል (Heaton 1990) ካሉት ሃሳብ ይሰማማል፡፡ከዚህ በመቀጠል ተጠኚ ተማሪዎች ቃላት አጠቃቀምን በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቃቸው የሰጡትን መረጃ ትንተና ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ 6፡-ቃላት አጠቃቀም በተመለከተ ከተማሪዎች ምላሾች የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምለሾች አመራጮች | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 3 | አንቀጽ በሚጽፍበት ጊዜ ተገቢ የሆኑ ቃላት በተገቢ ቦታቸው ለመጠቀም እጠነቀቃለሁ | በጣም ዝቅተኛ | 8 | 12.3 | 7 | 10.76 |
| | | ዝቅተኛ | 5 | 7.7 | 5 | 7.7 |
| | | መሀከለኛ | 14 | 21.5 | 20 | 30.8 |
| | | ከፍተኛ | 20 | 30.8 | 31 | 47.69 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 18 | 27.7 | 2 | 3.07 |
| 4 | መምህሬ የጽህፈት ትምህርተ ሲያስተምሩና አንቀጽ /ድርሰት ሲያጽፉ ስለ ቃላት አጠቃቀም በሚገባ አስረድተውኛል | በጣም ዝቅተኛ | 4 | 6.15 | 3 | 4.6 |
| | | ዝቅተኛ | 8 | 12.30 | 11 | 16.9 |
| | | መሀከለኛ | 10 | 15.4 | 17 | 26.15 |
| | | ከፍተኛ | 21 | 32.2 | 20 | 30.8 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 22 | 30.8 | 10 | 15.4 |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዣዊ መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው “አንቀፅ በምጽበት ጊዜ የሆኑ ቃላት በተገቢ ቦታቸው ለመጠቀም እጠነቀቃለሁ” ብሎ ለቀረበው ጥያቄ ከመንግስት ትምህርት ቤት ከመለሱት 33(50.76%) ያህል ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ሲሉ ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ 38(58.5 %) የሚሆኑት ከፍተኛ ፣በጣም ከፍተኛ በማለት ምላሽ ሰጠተወዋል፡፡በተቃራኒ ደግሞ 27(41.5 %) የሚሆኑት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለተነሳው ጥያቄ ዝቅተኛ ምላሽሰ ሲሰጡ፣ 12(18.46 %) ያህሉ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በበኩላቸው ዝቅተኛ በማለታቸው ምላሾቻቸው ገልጽዋል፡፡
ከቃላት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በተራ ቁጥር 4 ላይ “መምህሬ የጽህፈት ትምህርት ሲያስተምሩ አንቀጽ /ድርሰት ሲያጽፉስ የቃላት አጠቃቀም በሚገባ አስረድተውኛል “በማለት ለቀረበው ጥያቄ 53(78.4 %) የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሀከለኛ፣ ከፍተኛእና በጣም

ከፍተኛ ሲሉ 47(72.4 %) ያህሉ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በበኩላቸው መሀከለኛ፣ ከፍተኛእና በጣም ከፍተኛ የሚሊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል 14(21፣5) የሚሆኑት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ዝቅተኛ ሲሉ ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ 12(18.45%) ያህሉት ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ዝቅተኛ ሲሉ ገልጽዋል፡፡

ባአጠቃላይ ከመረጃ ትንተና መመልዕክት እንደሚቻለው ከመንግስት ትምህርት ቤትና ከግል ትምህርት ቤቶች የተሳተፉ አብዘኛዎቹ ተማሪዎች አንቀጽ በሚጽፍበት ጊዜ ተገቢን የሆኑ ቃላት በተገቢ ቦታዎች ለመጠቀም እንደሚጠነቀቁ እና መምህራኖቻቸው የጸህፈትትምህትርት ሲያስተምሩትና አንቀጽ /ድርሰት ሲያስፉት ቃላት አጠቃቀም በሚገባ እንዳስተማራቸው ያሳያል፡፡

ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘውም መረጃ ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ለመምህራኑ የቀረበው ጥያቄ "ተማሪዎች ድረሰት አንቀጽ በሚጽፉበት ወቅት ተገቢ ቃላትን በተገቢ ቦታ ስለ መጠቀማቸው ያለዎት እምነትዎ ምን ያህል ነው" የሚል ነበረ፡፡መምህራኑ ሲመልሱ መጣም ጥቅት ተማሪዎች ናቸው በተወሰነ ደረጃ ቢሆንም በቃላት አጠቃቀም ግንዛቤ ያላቸው፤ በተላይም ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ በግል ትምህርት ቤቶች ማለትም ለምሳሌ አድቨንትስት እና ሙሉ ወንጌል ትምህርት ቤቶች ተምረው የመጡት ተማሪዎች የተሸለ ዝንባሌ አላቸውና እነሱ መሞከራቸውን ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም "ተማሪዎች ድርሰቶቻቸውን /አንቀጾቻቸው በሚጽፉበት ወቅት ሰለቃላት አጠቃቀም ትኩረት እንዲያደጉት በክፍልዎ ትምህርት አክለው ያስተማሩት ምን ምን ያካተተ ነበር" የሚል ጥያቄ ለመምህራን ቀርቦ ነበር ፡፡ለዚህ መጠይቅ መምህራኑ የሰጡት መልስ ቃላት በጽህፈት ውስጥ ያለ ተገቢ ቦታ ከተጠቀምን የተፈለገውን መልእክት ማስተላለፍ አይችልምና አንባቢውን ያደናግረዋል ፡፡ስለሆነም ተማሮቻችን ስለአንቀጽ ስናስተምራቸው ቃላት ለጾታ፣ለመደብ ፤እድሁም ለብዙና ለነጠላ ቁጥሮች እንዴት እንደሚንጠቅምባቸው አስተምረዋቸዋለሁ፡፡የሚል ነው፡፡

ሀሳብን በጽሑፍ አቀናብሮ ለማቅረብ የሚንጠቀማቸው ቃላት ወሳኝና የደራሲ ቀኝ እጅ ናቸው በመላት አማረ (1986) ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ጥናት እንደ መረጃ በቀረበው አብዘኛው የተማሪዎቹ ጽህፈት ውስጥ ቃላት ከቆመላቸው አላማ አፈንግጠው ሲወጡ ተስተውሏ፡፡

## 4.4.በተጠቀሱ ትምህርት ቤች የሚጉኙ ተማሪዎች በጻፉት አንቀጽ የሥረዓተ - ነጥብ አጠቃቀም

በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ስርዓተነጥብ የምጠቀመው ለሁለት አላማ ነው፡፡አንደኛው የምንጽፈው ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ቃላት ፣ሀረጋትንና አረፍተ ነገሮች አሰዳደር ሥርዓትን የጠበቁና ተነባቢ እንደሆኑ ለማድረግ፣ሁለተኛው አላማ ደግሞ የጻፋነው ጽሑፍ መልእክት ለአንባቢዎች በተገቢን መንገድ እንዲደርስ ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን በተገቢው ቦታ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አለመጠቀም ወይም ፈጽሞ ሥርዓተ ነጥብ አለመጠቀም የጽሑፋችን መልዕክት ባሰበነው መልኩ ለአንባቢ እንዳይደርስ ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ጸሐፊው የጻፈውን መልእክት አንባቢ እንዲረዳለት ለማድረግ በተገቢው ቦታ ተገቢ ሥርዓተ ነጥቦችን መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የአንባቢን የማንበብ ስሜት ሊቀንስ እንደሚችል (Dulay.et.at) 1982 ገልጸዋል፡፡ ሥርዓተ ነጥቦች የጽሑፍ መሪ ምልክቶች ናቸው፡፡ ይህም ሲባል ጽሕፈት እንደ ንግግር በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ምልክቶች ሊታጀብ አይችልም፡፡ የጽሑፉን መልእክት ግልጽ ለማድረግ የምንጠቀመው ሥረዓተ ነጥቦችን ነው፡፡ ስለዚህ ሥርዓተ ነጥቦች ስንጠቀም በአግባቡ መጠቀም በሚገባን ቦታ ላይ መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ ጥናት በስህተትነት ከታዩት ስህተቶች ውስጥ ሰፊው የሥርዓት ነጥብ አጠቃቀም ስህተትነው፡፡ ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የታዩት የአራት ነጥብና የነጠላ ሰረዝ አጠቃቀም ስህቶች ሲሆኑ አልፎ አልፎም ሌላን በነጠላ ሰረዝና በአራት ነጥብ ተክቶ መጠቀምም ተሰተውሏል፡፡

መረጃውም በዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### ሠንጠረዥ 7፡-በሁለት ነጥ አጠቃቀም ላይ የተፈፀመ ስህተት መረጃ

| ስህተት | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | | | | | የመንግስት ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሁለት ነጥብ | የአን ቀጽ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካ ይ ቃላት | የስህተ ት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የአንቀጾ ችብዛት | የቃላት ብዛት | አማካ ይ ቃላት | የስህ ተት ብዛት | አማካ ይ ስህተት | ስህተተት በመቶኛ |
| | 121 | 13320 | 110 | 136 | 1.2 | 1.02% | 121 | 13535 | 111.9 | 153 | 1.26 | 1.13% |

ከላይ በቀረበው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የግ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ 136 የሁለት ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ሲቆጠሩ የመንግስት ትምህርት ቤት

ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ ደግሞ 153 ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ በፍት የተሠራበትን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሰረት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአንቀጾቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ የሁለት አጠቃቀም ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከአንቀጽ ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑ ለማወቅ ተችለዋል፡፡ በዚህ መሰረት 136 ለ 121 ስናካፍለው 1.02 አማካይ ስህተት እናገኛለን፡፡ ተማሪዎቹ አንቀጽ የጻፉባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው 110 መሆኑ የታወቃል፡፡

በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት*100 = 1.2*100=1.02 %

አማካይ ቃላት 110

ተጠኚ ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ጽሁፎች መመልከት እንደተቻለው ከቃልና ቃል መካከል መግባት ያለበት ሁለት ነጥብ ያልገባበት ተስተውሏል፡፡ ጢቅቶቹን ለአብነት ያህል ፡-

“----አንድወጣትተማሪ እርሱ የሁለቱ ተረካብ ብሆን----“

“-----በምድርላይከክርስቶስ ውጭ/ በስተቀር ስለፍቅር ---“

“---ጎበዝተማሪ ማለትየሚያጠና የሰው ምክር የሚቀበል-----“

ከምሳሌው መረዳት የሚቻለው የጻፉት ዓረፍተ ነገር መሀል ሁለት ነጥብ አለመግባቱነው በሌላ በኩል በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል፡፡በመሆኑም ተማሪዎቹ በጻፉት አንቀጽ ውስጥ 153 ሲካፈል 121 =1.13% አማካይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አንቀጽ የጸፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለጸው 111.9 ነው፡፡

በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት*100 = 1.26*100=1.13%

አማካይ ቃላት 111.9

በአጠቃላይ የሁለት ነጥብ አጠቃቀም በኮምፒውተር ጽህፈት ጊዜ ለሁለት ነጥብ ቦታ እየተተው መፃፍ ይቻላል፡፡ በእጅም ጽህፈት ቢሆን እንዱሁ ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን በዚህ መንገድ መጠቀም አረፍተ-ነገሮቹን አንብቦ ለመረዲት በጣም ያስቸግራል፡፡

## ሠንጠረዥ 8፡-በነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ላይ የተፈፀመ ስህተት መረጃ

| ስህተት | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | | | | | የመንግስት ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የአንቀጽ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የአንቀጾች ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተተት በመቶኛ |
| | 121 | 13320 | 110 | 81 | 0.67 | 0.61% | 121 | 13535 | 111.9 | 108 | 0.89 | 0.79% |

ከላይ በቀረበው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የግል ትምህርት ቤት የተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ ውጤት 81 የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ሲቆጠሩ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ ደግሞ 108 ስህተቶች ተቆጥረዋል፡፡ በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመተኛ ለማወቅ ከዚህ በፊት የተሰራበትን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል፡፡በዚህም መሰረት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአንቀጾቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ ነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከአንቀጽ ቁጥር ጋር በማከፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት 81 ለ 121 ስካፍለው 0.67 አማካይ ስህተት እናገኛለን፡፡ ተማሪዎቹ አንቀጽ የፃፈባቸው ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 110 መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}*100}{\text{አማካይ ቃላት}} = \frac{0.67*100}{110}=0.61\%$$

በሌላ በኩል በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪወች በፃፏቸው አንቀጾች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል፡፡ በመሆኑን ተማሪዎች በፃፉት አንቀጽ ውስጥ 108 የሚሆኑ የነጠላ ሠረዝ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለአንጹ ቁጥር በማካፈል ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት 108 ለ 121 0.89 አማካይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንቀጽ የጻፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 111.9 ነው፡፡

በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት * 100 =0.89*100= 0.79%

አማካይ ቃላት 111.9

ተተኳሪ ተማሪዎች ከጻፏቸው ሁለት አንቀጾች መገንዘብእንደተቻለው በዝርዝ በሚጠቀሱ ቃላት መካካል መግባት ያለበት ነጠላ ሠረዝ ያልገባበት መሆኑ ተስተውሏል፡፡ የተወሰኑት ለአብነት እንመልከት፡-

“--- ጎበዙ ተማሪ ትምህርት ቤት ከመምጠቱ በፊት ደፍተሩ መጻፉን እስክብርቶ እና መስመሪያዎቹን ቦርሳው አስተካክሎ ቁርስ በልቶ ይንፌርሙን--“

“---ለሰላም ለፊትህ ለህዝቦች ነፃነት”

ከላይበቀረቡት የተማሪ ጽሑፎች ውስጥ ከነጠላ ሰረዝ ስህተት ባሻገር ሌሎች ባዕድ ቃላት (ይንፌርሙን) አጠቃቀም ችግር መኖሩም መመልከት ተችሏል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች ጽሕፈት በሚያከናወኑበት ወቅት የሚፈጠረው አንዱ ችግር ሌላው እየጎተተ የጻፉት ሀሳብ ለአንባቢ ግራ እንድጋባ ያደረገዋል፡፡

ሠንጠረዥ 9፡- በአራት ነጥብ አጠቃቀም ላይ የተፈፀሙ ስህተት መረጃ

| ስህተት | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | | | | | የመንግስት ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የአን ቀጽ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካ ይ ቃላት | የስህተ ት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የአንቀጾ ችብዛት | የቃላት ብዛት | አማካ ይ ቃላት | የስህ ተት ብዛት | አማካ ይ ስህተት | ስህተተት በመቶኛ |
| | 121 | 13320 | 110 | 95 | 0.78 | 0.70% | 121 | 13535 | 111.9 | 88 | 0.72 | 0.64% |

በሠንጠረዥ ሰባት መረጃ መሰረት በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ውስጥ ከተዘረዘሩት ንዑስ የስህተት ምድቦች የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተት ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ ይገኛል፡፡በአንቀጾች ውስጥ ከታዩት ስህተቶች መካከል 95 የሚሆኑ በዚህ ምድብ ውስጥ የገኛሉ፡፡የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ቀመር ተግባራዊ በማደረግ ለማስላት ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአንቀጾቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን

ከአንቀጽ ቁጥር ጋር  በማካፈል አማካይ ስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት 95 ለ121 ስናካፈል 0.78 አማካይ ስህተት  እናገኛለን፡፡ ተማሪዎቹ አንቀጽ የጻፈባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው 110 መሆን ይታወቃል፡፡ በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት * 100 = 0.78*100= 0.70%

አማካይ ቃላት                111.9

የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከፃፏቸው አንቀጾች ውስጥ ከተገኙ ጥቂቶች ለአብነት

"--- ታየ ሀዝባውነት ዳር እስከዳር በርቶ"

"--- በኩሊነት በፍቅር ቆመናል  በነደነት"

"---እንጠብቂሻለ አለብን ሀደራ"

በሌላ በኩል በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪወች በፃፏቸው አንቀጾች ውሰጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል፡፡ በመሆኑን ተማሪዎች በፃፉት አንቀጽ ውስጥ 88 የሚሆኑ የነጠላ ሠረዝ  አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለአንጹ ቁጥር በማካፈል ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት 88 ለ 121  0.72 አማካይ ስህተት መሆኑ ተረገግጧል፡፡ አንቀጽ የጻፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 111.9 ነው፡፡

በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት * 100 =0.72*100= 0.64%

አማካይ ቃላት                111.9

እነዚህ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ  ከተገኙ ጥቂቶቹ ለአብነት፡-

"--- አረካ በምትባለ ከተማ ትወለጀ ካደኩኝ 13 ዓመት ሞላኝ

" ---የተፍጠሮ ፀጋ የጀግና ህዝብ እናት

" ---እኔ ተማር ነኝ የተወለደኩኝ አ/ም ነው

" ---የህይወት ታርክ ይህን ይመስላል--"

ሠንጠረዥ10፡-የሥራዓተ ነጥብ አጠቃቀም ከተጠኚ ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምለሾች አመራጮች | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | አንድን ሀሳብ በጽሑፍ ሳሰፍርመልዕክቴን ለማስተላለፍ ስርአተኛ ከፍተኛ ሚና አለቸው | በጣም ዝቅተ | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| | | | 1 | 1.5 | 7 | 10.76 |
| | | ዝቅተኛ | 5 | 7.7 | 8 | 12.3 |
| | | መሀከለኛ | 4 | 6.15 | 3 | 4.6 |
| | | ከፍተኛ | 37 | 56.9 | 32 | 49.2 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 14 | 21.2 | 15 | 23 |
| 6 | መምህሬ የጽህፈት ትምህርተ ሲያስተምሩኝ ስለ ስርአተ ነጥቦች ሚና አስረድተውኛል | በጣም ዝቅተኛ | 4 | 6.15 | 3 | 4.6 |
| | | ዝቅተኛ | 13 | 20 | 11 | 16.9 |
| | | መሀከለኛ | 5 | 7.7 | 17 | 26.15 |
| | | ከፍተኛ | 21 | 32.2 | 20 | 30.8 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 22 | 30.8 | 14 | 15.4 |
| 7 | እኔ በምጽፉቸው አረፍተነገሮች፣አንቀጾች ወይም ድርሰቶች ተገቢ ስረአተ ነጥብ በተገቢ ቦታ ለመጠቀም አያቅትም | በጣም ዝቅተኛ | 28 | 43 | 21 | 32.3 |
| | | ዝቅተኛ | 26 | 40 | 19 | 29.2 |
| | | መሀከለኛ | 2 | 3 | 4 | 6.2 |
| | | ከፍተኛ | 4 | 6.2 | 10 | 15.4 |
| | | በጣም ከፍተኛ | 5 | 7.6 | 11 | 16.9 |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዣዊ መረጃ ለመረዳትበተነሳ ጥያቄ ቁጥር አምስት “አንድን ሀሳብ በጽሑፍ ሳሰፈር መልዕቴን ለማስተለለፍ ስርአተ ነጥቦች ከፍተኛ ሚና አለሳቸው”ለሚለውከተሰጠው የምላሽ ለመረዳት እንደሚቻለው ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ በድምሩ 55(84.25%)የሚሆኑት በመሀከለኛ፣ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ምላሽ ስሰጡ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ 46( 81%) በመሀከለኛ፣ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ምላሽ ገልጸዋል፡፡በተቃራኒው ሲታይ አንድን ሀሳብ በጽሑፍ ሳሰፍር መልዕቴን ለማስላለፍ ስርዐተ ነጥቦች ከፍተኛ ሚና አላቸው ለሚለው ሀሳብ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት ከመንግስት ትምህርት ቤት 15(19%) ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 6(15.75%) መሆናቸው ነው፡፡

በጥያቄ ቁጥር ስድስት ላይ “መምህሬ የጽሕፈት ትምህርት ሲያስተንሩኝ ስለስርአተ ነጥቦችን አስረድውኛል” የሚለው ቀርቦ 46(7.8%) ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሌሎች 51(78.46) ደግሞ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመሀከለኛ፣ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ምላሽ ሰጥተተዋል፡፡ ከዚህ በሌላ በኩል 17(26.15%) ከግል ትምህርት ቤት 14(21.5%) ተማሪዎች ከመንግት ትምህርት ቤት አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው “እኔ በምጽፋቸው አረፍተ ነገሮች ፣አንቀጾች ወይም ድርሰቶች ተገቢ ስርአተ ነጥብ በተገቢ ቦታ ለመጠቃም አያቅተኝ” ብሎ ለተነሳው መጠይቅ ከግል ትምህርት ቤት 54(83%) በጣም ዝቅተኛ እና ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሲሰጡ ከመንግስት ተረምህርት ቤት ደግሞ 40(61.5%) የሚሆኑት በጉዳይ በጣም ዝቅተኛ እና ዝቅተኛ ሠንዘረዋል፡፡ ከዚህ ጥያቄ ሳይወጣ የመንግስት ና የግል  ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ በጣም ከፍተኛ ምላሽ የሰጡት ከመንግስት ትምህርት ቤት 11(16.9%) ምላሾች ሲሆኑ ከግል ትምህርት ቤት ደግሞ 5(7.6%) መሆናቸውን የሠንጠረዡ መረጃ ያረጋግጣል፡፡ለመምራን ከቀረቡት ቃለለ-መጠይቅቆች በመጨረሻ የቀረበው ጥያቄ የክፍልዎ ተማሪዎች በአንድ ርዕስ ዙሪያ በየግላቸው አንቀጽ ሲጽፉ በአንቀጾቸቸው ጎልተው የሚታይባቸው ስህተቶች ምንድር ናቸው? የሚል ነበር ፡፡ ከመምህራን የተገኙ መልሶች መካከል አንዱ በርካታ ግድፈቶች ይስተዋላል፤የቃላት ምርጫ ፣የቃላት መዋቀር ፣ዐረፍተ ነገሮች አሰክከ ስህተቶች ውስጥ ይገኛሉ የሚል ነው፡፡ ሌላው ምላሽ ተማሪዎች የእጅ ጽሑፍ ለአንባቢ እጅግ በጣም ፈተና የሆንበታል፡፡ የፊደላት አጣጣል ወይም ቅርጽ እንኳን ለመለየት ያዳግታል፡፡ከዚህ ጋር ተያያዞ ሌላው መምህራኑ የሰጡት ምላሽ የስርዓተ ነጥብ ጉዳይ ሲሆን ፤የተማሪዎች ጽሑፍ ውስጥ ተገቢ የስረዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች በስፋት የስተዋላሉ፡፡ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ በተገቢ ስፍራ ሳይገባ መቅረት አሊያም ምንም ዓይነት ስረዐተ ነጥብ ከቶውን ያለመጠቀም ይታያል፡፡

## 4.5 በተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች የዐረፍተ ነገር አጠቃም ሁኔታ

በዚህ ክፍል ተመሪዎች በጻፏቸው አንቀጽ ውስጥ የሚታዩ የዐረፍተ ነገር ስህተቶችን በመቁጠር የሚከተለው መረጃ ተተንትኗል፡፡ከላይ የተገለጹት ስህተቶች ለአሰራር ያመቹ ዘንድ በአንድ ክፍል በመመደብ ትንተና ተደርጓል፡፡ ስህተቶች ማለትም የጾታ፣የቁጥር ፣የመደብ አጠቃቀም በተመለከተ ነው፡፡

## ሠንጠረዥ 11፡- የተጠኻዎች ዐረፍተ ነገት አጠቃቀም ስህተት መረጃ

| ስህተት | የግል ት/ቤት ተማሪዎች | | | | | | የመንግስት ት/ቤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የአንቀጽ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የአንቀጾችብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አማካይ ስህተት | ስህተተት በመቶኛ |
| | 121 | 13320 | 110 | 58 | 0.48 | 0.43% | 121 | 13535 | 111.9 | 66 | 0.54 | 0.49% |

ሠንጠረዡ እንደሚያሳየው ከስህተት ምድቦች ውስጥ አንዱ ጠዐረፍተ ነገር አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡ የዐረፍተ ነገር አጠቃቀም ስህተት በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንቀጽ ውስጥ 58 የሚሆኑት ቁጥር የያዘ ነው፡፡የዚህ የስህተት ምድብ አማካይ መጠኑ ተሰልቶ 0.48 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ ደግሞ 0.43 ነው፡፡ ይህ ማለት የስህተትአይነቱ በአንድ አንቀጽ ውስጥ 0.43 ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል ማለት ነው፡፡

ስህተቱ በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

አማካይ ስህተት * 100 =0.48*100= 0.43%

አማካይ ቃላት 110

ከተማሪዎች አንቀጾዐች ውስጥ ከተስተዋሉ የዐረፍተ ነገር ስህተቶች የመደብ ስህተት ለአብነት እንድሚከተለው ቀርቧል፡-

-----ስምንተኛ ክፍል በአረካ ድል በህብረት የተማርኩ ሲሆን 9ኛ ክፊርል አረካ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባሁ

---እድሜዬ ለትምህርት ስደርስ በአቅራቢያው በሚገኝ ዋዱ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመማር ገባሁ ---እኔ ከአባቴ ና ከእናቴ በ1994 አ/ም ወላይታ ዞን በአረካ ከተማ ተወልጂያለሁ እንደዚሁም በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተፃፉት አንቀጾች ውስጥ የሚገኘውን የዐረፍተ ነገር አጠቃላይ ስህተት 66 ነው፡፡ የዚህ የስህተት አማካይ መጠኑ ተሰልቶ 0.54 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ ደግሞ 0.49 ጊዜ ተደጋግሞ ይገኛል፡፡ማለት ነው፡፡ የዚህ ስህተት መቶኛ ስለቱም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

አማካይ ስህተት * 100 =0.54*100= 0.49%

አማካይ ቃላት 111.9

በእነዚህ ተጠኚ ተማሪዎች ከተፈጸሙት ዐረፍተ ነገር ግድፈቶችን ለአብነት ስንመለከት፣

----ዱቦ ትምህርት ቤት ለኔ ዘንድሮ አድስ ነው መጀመርያ እኔ ያገኝሁ ጓደኞች ሚጠና ፉጤ ነው

--ከጓደኞቸ ጋር ከትምህርት ቤት ውጭ በጋራ ?ቤት ስራችንን መስራትና ማጥናት ጀመርኩ

---የበተሰብ ጫና ለኔ አይበዛመበትም

እነዚህ ሁለቱም ተጠኚዎች ከጻፏቻቸው አንቀጾች ውስጥ የተገኙት ስህተቶች አብዘኛው የመደብና የቁጥር ብሎም የመሰሪያ አንቀጽ ስህተቶች ናቸው፡፡

4.6 የሀለት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች መካከል የጽሕፈት መመሳሰል እና ወይም መለያየት መኖሩ ለማረጋጥ

በዚህ ንዑስ ክፍል አራተኛውን የጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ ከሁለቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በተጻፏቸው አነቀጾች ላይ በተደረገው ፍተሻ የየትኞች አንቀጾች ውስጥ መጠነኛ እደተፈጠሩ እና የትኞች ተማሪዎች አንቀጽ በመፃፍ የተሸለ እንዳላቸው ለመለየት የሚያስችል ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ሠንጠረዥ 12፡- በተተኳሪ ተማሪቸዎች መካከል የጽሕፈት ስህተቶች መመሳልና መለያየት

| ተ/ቁ | የግል ትምህርት ቤት | | | የመንግስት ትምህርት ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስህተት የፍተ ነገተመዘገበበት ንዑስ ክሂል | አጠቃላይ ስህተት ብዛት | ስህተት በመቶኛ | አጠቃላይ ስህተት ብዛት | ስህተት በመቶኛ |
| 1 | የሆሄያት ቅርጽ | 36 | 0.27% | 59 | 0.47% |
| 2 | የቃላት አጠቃቀም | 37 | 0.27% | 46 | 0.49% |
| 3 | የስርአተ ነጥብ አጠቃም | | | | |
| ሀ | ሁለት ነጥብ | 136 | 1.02% | 153 | 1.13% |
| ለ | ነጠላ ሠረዝ | 81 | 0.61% | 108 | 0.79% |
| ሐ | አራት ነጥብ | 95 | 0.78% | 88 | 0.64% |
| መ | ዐረፍተ ነገር | 58 | 0.43% | 66 | 0.54% |
| | አጠቃላይ ድምር | 443 | 2.75% | 520 | 4.06% |

ከላይ ባለው ሠንጠረዥ መረጃ እንደተገለጸው የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ በተፈጸሙ የሆሄያት ቅርጽ፣የቃላት አጠቃቀም ሥርዓተ ነጥብ

ማለትም በነጠላ ሠረዝ ፣በአራት ነጥብ እና በዐረፍተ ነገር አጠቃቀም ስህተትች አንጻር የዱቦ እመቤታችን ቅድስት ማሪያም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ እውቀት ሲኖራቸው አጠቃላይ ሶስት መቶ ሰባት ስህተቶች ተቆጥሮባቸዋል፡፡የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች የተቆጠሩ አጠቃላይ ስህተቶች ሶስት መቶ ስልሳ ሰባት ነው፡፡ ይህ ማለት በእነዚህ ተማሪዎች የተመዘገቡ አጠቃላይ ስህተቶች ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስህተቶች ጋር ሲነፃፀር በስልሳ ብልጫ አለው፡፡

## 4.7 የውጤት ማብራሪያ

- ይህ ጥናት በአረካ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ የግልና የመንግስት ትምህርት በቶች አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማረዎች የጽሕፈት ክሂል ንፅፅር ስለሆነ ከዚህ ጋር ተያይዞ የፅሕፈት ደረጃቸው ምን ላይ እንደሚገኝ እና የትኞቹ የተሻሉ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መለየት ነው፡፡በዚህ ክፍል የጥናቱ ውጤቶች ማብራሪያ በየዝርዝር አላማው አንጻር ቀርቧል፡፡
- አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽማቸው የሆሄያት ቅርጽ ስህተቶችን መለየት የሚለው ከጥናቱ ዝርዝር አላማዎች የመጀመሪያ አላማ ነው፡፡ ሁለቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በተሰጣቸው የጽሑፍ ፈተናዎች በጻፏቸው አንቀጾች የሆሄያት ግድፈቶች ተቆጥረዋል፡፡ በዚህ መሰረት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች 13320 ቃላትን ተጠቅመው በጻፉት 121 አንቀጾች ውስጥ 36 የሆሄያት ቅርጽ ግድፈቶች በመምህራን ከታረመው ፈተና የተገኙ ሲሆን የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው 13535 ቃላት ደግሞ 59 የሆሄያት ግድፈቶች ተመዝግበዋል፡፡
- ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ የሁለቱን ተተኳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መምህራኖቻቸው ስለ ጽሕፈት በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ስለሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የሆሄያት ቅርጽ እንዳስተማሯቸውና አንቀጽ/ድርሰት /በምጽፉበት ጊዜ ስለ ሆሄያት ቅርጽ ጥንቃቄ እንደሚያድረጉ ውጤቱ ያሳያል፡፡ ለመምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ የተገኘው ውጤት በበኩሉ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው ስለአንቀጽ አጻጻፍ ሲያስተምሩዋቸው የተሲተካከለ አንቀጽ/ድርሰት እንዲጽፉ የሚያግዟቸው የሀሳብ ፍሰት ፣የፊደላት ቅርጽን በአግባቡ በመጠቀም ፣የቃላት

አመራረጥ ሁኔታ እና የዐረፍተ ነገር አጻጻፍና የስርዓተ ነጥብ አግባብነት ያጠቃለለ ነው፡፡

- በክፍል ውስጥ በሚደረገው የጽሕፈት ልምምድ የመምህራኑ እገዛ በጣም አስፈላጊ መሆኑ አያጠራጥርም ፡፡ለዚህም Pincas (1982:18) ሲገልጹ ተማሪዎች በልምምድ ደረጃ ውስን ፅህፈትን ተለማምደው ቀስ በቀስ ወደ መሪ የፅህፈት ክንውን ደረጃ ይሸጋገራሉ ፡፡
- እንደዚሁም Celece Murcia, (1991:236) ተማሪዎች የፊደልን ቅርጽ በመለየት ቃላትን መስርተው የቃላትን ምርጫና አጠቃቀም በማውቅ ሀሳባቸውን በተገቢው ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች ማስተላለፍ ይችላሉ ያሉትን ያጠናክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች የጽሑፍ ፈተና የታረመበት የተግባር ውጤት ተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ እና የመምህራን የቃል -መጠይቅ ውጤት ጋር ይቃረናል፡፡
- ተማሪዎች በጻፉት ጽሕፈት ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች መተንተን የሚለው የጥናቱ ሁለተኛ ዓላማ ነው፡፡ የተተኳሪ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው ፈተናዎች ውስጥ የተሟላላቸው ቃላት መካከል የተገኙ ስህትቶች በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች 37 ነው፡፡በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፃፏቸው አንቀጾች ውስጥ የሚገኙ የስህተት ብዛት 46 ነው፡፡ በዚህ ንጽጽር የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በተጠቀሙት ቃላት አነስ ያለ ስህተት አስመዝግበዋል፡፡
- ይህ በእንዲህ እንዳለ የተማሪዎች የጽሑፍ ጥያቄ ውጤት ግን ሁለቱም ተጠኚ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በክፍል ጊዜ ትምህርታቸው መምህራኖቻቸው አንቀጽ በሚጽፉበት ጊዜ ተገቢ የሆኑ ቃላት በተገቢ ቦታቸው ስለመጠቀም በሚገባ ማስረዳትታቸውን ያሳያል፡፡
- መምህራን የሰጡት ቃለ-መጠይቅ ውጤት በበኩሉ ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ በግል ትምህርት ቤቶች ተምረው ከመጡት ጥቂት ተማሪዎች በጽሑፎቻቸው በንጽጽሩ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ዝንባሌ እንዳላቸው ያሳያል፡፡ሀሳብን በጽሑፍ አቀናብሮ ለማቅረብ የመረጥናቸው ቃላት ወሳኝና የደራሲ ቀኝ እጅ ናቸው በማላት አማረ (1986) ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት እንደ መረጃ በቀረበው አብዘኛው የተማሪዎች ጽህፈት ውስጥ ቃላት ከቆሙላቸው ዓለማ አፈንግጥው የወጡ መሆናቸው ተስተውሏል፡፡

- ሶስቱ የዚህ ጥናት ዓላማው ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ የተጠሟቸውን ስርዓተ ነጥቦችን መፈተሸና ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር መጠቀም ያለመጠማቸውን መለየት የሚል ነው፡፡
- በአንድ ጽሑፍ ወስጥ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ መጠቀም በሚጻፈው ጽሑፍ ውሰጥ ያሉ ቃላት ፣ሀረጋትና ዓረፍተ ነገሮች አሰዳደር ሥርዓትን የጠበቁና እንዲሆኑ ለማድረግ እና የተጻፈው ጽሑፍ መልዕክት ለአንባቢያን በተገቢው መንገድ እንዲደርሰው ማድረግ ነው፡፡ ጥናቱ ከተካሄደባቸው የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በፃፏቸው አንቀጾች ውስጥ 136 ሁለት ነጥብ 81 የነጠላሠረዝ እና 95 የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች የተገኙ ሲሆን አጠቃላይ 312 የስረዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ተስተውለዋል፡፡
- እነዚህ የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ 153 ሁለት ነጥብ 109 ነጠላ ሠረዝ እና 88 የአራት ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረው በድምሩ 350 የስረዐተ ነጥብ ስህተቶች ተገኝተዋል፡፡ይህ ደግሞ በተወሰነ ደረጃ ብሆን የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያነሰ የስረዓተ ነጥብ ስህተት በማስቆጠራቸው የሻለ ዕውቀት መኖራቸው አሳይቷል፡፡ በጻፏቸው አንቀጾች ውሰጥ ከተገኙ የዐረፍተ ነገር አሰካክ ስህተቶች አብዘኛው የመደብ ፣የቁጥር እና የማሰሪያ አንቀጽ ስህተቶች መሆናቸው መምህራን ከረማቸው ፈተና ልገኝ ችሏል፡፡
- ተማሪዎች የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት እንደሚያመለክተው አንድ ሀሳብ በጽሑፍ ሲሰፍር መልዕክቱን ለማስተላለፍ ሥርዓተ ነጥቦች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡መምህራን በጽሕፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለሥርዓተ ነጥቦች ሚና ማስተማራቸው ውጤቱ ይገልጻል፡፡
- ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኘ ውጤት የሚያሳየው ተማሪዎች በሚፈጽሟቸው የእጅ ጽሑፍ ተግባር ውሰጥ የቃል አመራረጥ ፣የቃላት መዋቀር ፣ዐረፍተ ነገሮች አሰካክ ስህተቶች መገኘቱ ለአንባቢ እጅግ በጣም ፈተና ይሆንበታል፡፡ የፊደላት አጣጣል /ቅርጽ/ እንኳን ለመለየት እንደሚያዳግት ያሳያል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ተገቢ የስረዓተ ነጥብ አለመጠቀም ስህተቶች በስፋት እንደምስተዋሉ ተጠቁሟል፡፡ይህ ውጤት እነ Dulay .et.al (1982) ከሚሉት ሀሳብ ይስማማል፡፡ እነርሱ እንደሚገልጹት ጸሐፍው የጻፈውን መልዕክት አንባቢ እንደረዳለት ለማድረግ በተገቢ ቦታ ተገቢ ሥርዓተ ነጥቦችን መጠቀም የኖርበታል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የአንባቢን የማንበብ ስሜት ሊቀንስ ይችላል፡፡

- አራተኛውና የመጨረሻው የዚህ ጥናት ዓላማ ከሁለት ተተኳሪ ተማሪዎች መካከል የጽህፈት ስህተት መመሳሰል /መለያየት /መኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡

የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውስጥ በተፈጸመው ሆሄያት ቅርጽ፣የቃላት አጠቃቀም ፣የስርዓተ ነጥብ ማለትም በነጠላ ሠረዝ ፣በአራት ነጥብ እና በዐረፍተ ነገር አጠቃቀም ስህተቶች ሲነጻጸሩ የዱቦ እመቤታችን ቅድስት ማርያም የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ ዕውቀት አላቸዉ፡፡ የፈጠሩት አጠቃላይ ስህተት ብዛት ሶስት መቶ ሰባት ሆነው የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚ ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች የተቆጠሩ አጠቃላይ ስህተቶች ሶስት መቶ ስልሳ ሰባት ነው፡፡ ይህ ማለት የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያስመዘገቡት አጠቃላይ ስህተቶች ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ካስመዘገቡት ስህተቶች ጋር በስልሳ ብልጫ መኖሩን ነው፡፡

በመሆኑም የግል ትምህርት ቤት ተማረዎች በተደረገው ጥናት በቀረበላቸው የጽሑፍ ፈተና በጽሑፍ መጠይቅና ከመምህራን በተገኘው ቃለመጠይቅ ውጤት በጽሕፈት ክሂሎታቸው ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሄ ሐሳብ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው በአረካ ከተማ አስተዳደር አፋቸውን በወላይትኛ ቋንቋ የፈቱ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በጽሕፈት ክሂልማነጻጸር ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎች ለዚህ ጥናት ግብ መምቻ ሆነው ቀርበዋል፡፡ከዚህ ጋር ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎች ለዚህ ጥናት ግብ መምቻ ሆነው ቀርበዋል፡፡እነርሱም፡-

- አፋቸውን በወላይትኛ የፈቱ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች አንቀጽ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የሆሄያት ቅርጽ ስህተቶችን መለየት፣
- በተጠቀሱ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በጽሑፍ ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶችን መተንተን፣
- የተጠቀሱት ተማሪዎች በጻፏቸው አንቀጾች ውሰጥ የተጠቀሟቸውን ስርዓት ነጥቦችን መፈተሸና ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር መጠቀም ያለመጠቀማቸውን መለየት፣
- በሁለት ትምህርተ ቤቶች ተተኳሪ ተማሪዎች መካከል የክሂል መመሳሰል እናጋገወይም መለያየት መኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡
- ለታለሙት ዓላማዎች ስኬት ለማግኘት በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ አንቀጾች ፣ከተማሪዎች ጽሑፍ መጠይቆች ከአማርኛ መምህራኖቻቸው ከተገኙ ቃለ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን የሚከተሉት ግኝቶች ላይ ተደርሷል፡፡
- በመጀመሪያ የፊደላትን ቅርጽ አጠቃቀም በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተመዘገባቸው ስህተት መጠን በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪወዎች ከተመዘገበባቸው ስህተት ያነሰ ስለሆነ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሸለ የፊደላትን ቅርጽ ክሂል እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡
- በአንቀጾች ውሰጥ በተቆጠሩት የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የፈጸሙት ስህተት መጠን ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከተፈጸሙት ስህተት ያነሰ ስለሆነ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሸለ የቃላት አጠቃቀም መኖራቸው ተስተውሏል፡፡
- በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ በሶስተኛነት የተነሳው የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስሆን፣እነዚህን ነጠላ ሰረዝ እና አራት ነጥብን አጠቃቀምን ያጠቃልላሉ፡፡የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ አሁንም በግል ትምህርተ ቤት ተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ የተመዘገቡ

ስህተቶች መጠን በመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከተመዘገቡ ስህተቶች ያነሰ ስለሆነ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ከመንግስት ትምህርተ ቤት ተማሪዎች የተሸለ ክሂል መኖራቸው ታይቷል፡፡

- አራተኛው የዚህ ጥናት ጉዳይ የዐረፍተ ነገር አጠቃቀም ነው፡፡ ተጠኚዎች በጻፏቸው አንቀጾች የዐረፍተ ነገር ግድፈቶች ተስተውሏል፡፡ በተላይም የመደብ፣የቁጥርና አልፎ አልፎ የማሰሪያ አንቀጽ ስህተቶች ተቆጥረው የግል ትምህረት ቤት ተማሪዎች የተሸለ ክሂል ማስመዘገባቸው ተስተውሏል፡፡
- በአጠቃላይ በተደረገው ንጽጽር በሆሄያት ቅርጽ ፣በተገቢ ቃላት ፣በነጠላ ሰረዝና በአራት ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሸለ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብ

- ተማሪዎች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ እያሉ የፊደላት ቅርጽ፣የቃላት አመሰራረትን ፣የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምን ለይተው እንዲመጡ የሚያግዝ የማስተማሪያ ዘዴና የማስተማሪያ ቁሳቁስ በሚመለከተው አካል ብዘጋጅ ፡፡
- አጋዥ የአማርኛ ትምህርት የማስተማሪያ ቁሳቆሶች መኖር በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን ክፍተት ልያሟላ ስለምችል በየክፍል ደረጃው የሚዘጋጅበት ሁኔታ ቢኖር፡፡
- የመምህራን የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎችን የሚያሳትፍ፣የሚያዝናና እና ትምህርቱን እንደወዱ የሚያደረግ ቢሆን፡፡
- በየክፍል ደረጃው የቀረቡትን የዘቶች በተገቢወ ሁኔታ ለማስተማር ተመጣጣኝ ክፍለ ግዜ ቢሰጥ፡፡
- ተማሪዎች በትምህርታቸው ፣በሥነጽሁፍ እና በተለያዩ ቋንቋ ነክ ጉዳይ ላይ የሚሳተፉብትና የሚበረታቱበት ሁኔታ ቢኖር፡፡
- የጽህፈት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረትን ከሚጠይቁ የቋንቋ ክሂልች አንደ ነው፡፡ በመሆኑም
  ተማሪዎች ይህን ክሂሌ በአግባቡ እንዱያዲብሩትና ተገቢውን እውቀት እንዱጨብጡ

በመማር ማስተማሩ የሚደረገው የመምህራን ድጋፍና ክትትል በማያቋርጥ ሁኔታ መተግበር ቢቻል የተሻለ ነው፡፡

- በመሆኑም አማርኛ የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት  ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን

 በከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ክፍል ላይ የሚያዳብሩት ሳይሆን ከታች ከዝቅተኛ ደረጃ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ መምህራን ለዚህ ትምህርት ትኩረት ሰጥተው፣ በእቅድና በተደራጀ መልኩ የፊደላትን ስርዓት፣ የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የመሳሰለትን ለተማሪዎቻቸው ማስተማር ሲችሉ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩ የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማዳበር በምን አይነት መንገድ ትምህርቱ ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል? የሚለው ጉዳይ ሊይ ትኩረት ቢሰጡበት የተሻለ ይሆናል፡፡ ተማሪዎቹ ምን አይነት ተግባራትን ቢያከናውኑ የመፃፍ ክሂላቸውን ያዳብራለ? የሚለት ጉዳዮች ሊይ በደንብ መስራቱ ተገቢ ነው፡፡ እንዱሁም ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂላቸው ለሚፈጽሙት ስህተት እንዳት መረዳት እንዲለባቸውና ስህተታቸውን እንዳት ማስተካከል እንደሚገባቸው መምህራን ዴጋፍ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናሌ፡፡

- ስለሆነም በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የሚያሳየን ተማሪዎቹ በተሇያየ የጽህፈት ክሂል የተለያዩ ደረጃ ሊይ እንዲለ ነው፡፡ ለምሳላ በቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው አማርኛ የግልትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሻለ ሲሆኑ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ደግሞ አማርኛ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከመንግስት ትምህርት ቤት  ተማሪዎች የተሻለ መሆናቸውን ጥናቱ አመልክቷል፡፡ እንዱሁም ሁሇቱም ቡድኖች ያላቸውን የክሂል ክፍተት እንዱያጠቡ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ድጋፍና ክትትል ቢያርግ የተሻለ ይሆናል፡፡ ይሄውም መምህሩ ተማሪዎች የግልና የቡድን ስራ እንዱሰሩ በማድረግ አንደ ተማሪ ከሌላው እየተማረ የክሂል እውቀት ክፍተታቸውን የሚሞለበትን መንገድ ማመቻቸት አንደና ተመራጭ መንገድ ነው፡፡

- ሌላው ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ጫና ሳይፈጥሩ ተማሪዎቹ በፈለጉት ርዕስ ላይ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግና ድርሰቶችን አይተው ችግራቸውን እንዲቀርፉ ግብረ-መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
- በአጠቃላይ የተማሪዎችን የጽህፈት ልምድ ለማዳበር ደግሞ አሳታፍ የትምህርት አቀራረብ እና በቂ የልምምድ ጊዜ መኖር አለበት፡፡ ይህ ስሆን ተማሪዎች የሚሰጣቸውን የጽህፈት መልመጃዎች ለመሥራት ያላቸው ፍላጎት ይጨምራል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

ሀና ታምራት። (2003)። "በሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማረርኛ ጽህፈት ክሂል ኮርስ 2 የአቀራረብና አተገባበር ፍተሸ።"አ.አ.ዩ ለአማርኛ ማስተማር ማስተረስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)

ሰለሞን የውንስናሎሎቹ። (1994)።አማረኛን ስነ ዘዴ።አዲስ አበባ ፤እለኒ ማተሚያ ቤት።

ሰይድ ይመር (1993) "ዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መምሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን ይህ ፈት ትምህርት ይዘቶችንና ክንውኖች የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ ትግበራ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ የሂኒቲስ፤የቋንቋዎች ጥናት ፤የጆናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ፤የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር፤(ያልታተመ)።

ባዬ ይማም (2000)። የአማረኛ ሰዋሰው ።አዲስ አበባ ት.መ.ማ.ማ.ድ።

ቅድስት ማርያም ዩኒቨረሲቲ ኮሌጅ። (2008)። ትምህርትን የማስተማር ስነ-ዘዴአዲስ አበባ።ቅድስት ማርያም ዩኒቨረሲቲ ኮሌጅ።

አማረ ማሞ። (1986)። የሌብወሁጼ ዴርሰት አፃፃፍ መሠረታዊ መመሪያ። አዱስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ዴርጅት፡

ዳንኤል ተኸሉ (1998)።ሜላታት አመሃ ህራን አፈታትናን ክእለታት ቋንቋ መቐለ ፣ሕትመት ሜጋ መቐለ ።

Abiy Y.(2013) High school students writing skills and their English language proficiency as Predictors of their English language writing performance of Bahir Dar University.publisher ltd Faculty of humanities.Department of English Ethiopia J. Educ&sevol.9 no1 September 2013

Bayrne Donn.(1991). Teaching writing Skill l, Hong Kong Long man.

Celece Murela M. (ed).(!991) Teaching Engilish as a second language Boston .Hainle and Hainile publisher.

David Cross (1991) Hand book practical Language Teaching 1st Edition

Hedge T.(1988).writing Oxford university press.

Harmer, J. C. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* London: Longman Group, UK Limitted

Heaton, J. B. (1990). *Writing English Language Tests.* (3rd Edition), London: Longman Group, UK limited.

Narrish J. (1983). Language Learners and their errprs.Londn; Mcmillan publishers Ltd.

Norrish, J. (1990). *Language Learners and their Errors.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Nunnan,D.(1989) designing tasks for the communicative classroom.Cambrige Cambrige University.

Pincas A.(1982) Teaching English writing London ;Macmillan Publishers.

Pincas A,(1989).Teaching English writing London ,MCMillan.

Raimes, A.(1983) Techniques in the teaching Writing Oxford:Oxiford University Press

Richards J.(1990) .The language Teaching matrix. Cambridge cobridge university press.

Richards J and Renadaya. A (2002) Methodology in Language Teaching anAnthology or current practice Cambrige University Press.

Widdowson H.G (1985) Teaching Language as Communcation Oxford Oxford Univrsity oress.

Zamel, V. (1985). “Responding to Student Writing” TESOL Quarterly.191, (PP.79-101).

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂማንት፣የቋንቋ፣ጥናት ፣የጆርናልዝና ኮምዩንከሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለዲህረ ምረቃ ምርምር ለሚዘጋጅ ጽሁፍ በዘጠነኛ ክፍል የሚሞላ የፅህፍ መጥይቅ

ውድ ተማሪዎች ፡-

የዚህ መጥይቅ ዓላማ ፡-በአረካ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስትና የግል ትምህርት ቤት ወላይትኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል ችሎታ የትኞች ተሸለው እንደሚገኙ በማነፀባር ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ ፣ችግሩን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቂ አንብበው ተገቢውን መልስ በመመለስ ቀና ትብብሪችሁን እንድታደርጉ እጠይቆታለሁ፡፡ በመሆኑም ውድ የሆነው ጊዚያችሁን መስዋዕት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድምያ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** 1. በመጠይቁ ላይ ስም አይጻፍም

2.መጠይቁን ከሌላ ሰው ጋር ወይም ጓደኛ አይቶ መሙላት የጥናቱን ውጤት ሊያዛባ ስለምችል አይፈቀድም፡፡

ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

መመሪያ 1፡- ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ

1ፆታ-----------------------2.ዕድሜ ---------------- 3. ክፍል ደረጃ-------------------------------

4፣ የትምህርት ቤት አይነት ፡- ሀ/ የግል--------------ለ/የመንግስት ----------------

5.አፍ ከፈታህበት ሌላ የሚትናገረው ቋንቋ ካለ --------------6. አፍ የፈታህበት ቋንቋ ----------

7. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጀመርክበት ክፍል --------------------

መመሪያ 2፡- ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የቀረቡት ጥያቄዎች አራት አማራጮችን ይዘዋል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ነው የምትሉትን በመምረጥ በሳጥኑ ውስጥ “X” ምልክት በማድረግ አመልክት፡፡

1. በጣም ከፍተኛ 3. መሀከለኛ 4. ዝቅተኛ

2.ከፍተኛ 5. በጣም ዝቅተኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍሌ መምህር በጽህፈት ወቅት ስለምጠቀምባቸው የተለያዩ የቃላት ምርጫ አስተምረውኛል | | | | | |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ ሀሳብ ለመግለጽ ያለህ ፍላጎት | | | | | |
| 3 | መምህር አንቀጽ በሚጽፍበት ጊዜ ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀምና ስርዓተ ነጥቦችን በአገባቡ እንደጠቀም አሳይቶኛል | | | | | |
| 4 | የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙን ጊዜ ርዕስ የሚመርጥ እኔ ነኝ | | | | | |
| 5 | በአማርኛ ቋንቋ አንቀጽ /ድረሰት/በሚጽፊበት ጊዜ ለዓረፍተ ነገር አጠቃቀም ጥንቃቀ አደርጋለሁ | | | | | |
| 6 | በክፍሌ ውስጥ ይሁን ከክፍል ውጭ የሰራሁትን የጽህፈት መልመጃዎች መምህረ አርሞልኝ ማስተካከያ ይሰጠኛል | | | | | |
| 7 | በአማርኛ ድርሰት በምጽፍበት ጊዜ ስለፊደላት ቅርጽ ጥንቃቀ አደርጋለሁ | | | | | |
| 8 | መምህራችሁ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለው ብቃትና ዝግጅት ወይም በመጻፍ | | | | | |
| 9 | ሰዎች አማርኛ በመጻፍ ሂደት ስትሳሳቱ ያላቸው አሉታዊ ምላሽ | | | | | |
| 10 | የክፍሌ መምህር በጸህፈት ወቅት ስለምጠቀምባቸው የተለያዩ የፊደላት ቅርጽ አስተምረውኛል | | | | | |

## አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስ

**የሂማንት፣የቋንቋ፣ጥናት ፣የጆርናልዝና ኮምዩንከሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

***ለዲህረ ምረቃ ምርምር ለሚዘጋጅ ጽሁፍ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የፅህፈት ክሂል መፈተሻ ፈተና***

*ውድ ተማሪዎች !* *መመሪያ አንድ*

*የግል መረጃ ዕድሜ* ---------------------*የት/ቤት ስም*----------------------*የት/ቤቱ ዓይነት ሀ/የግል ለ/የመንግስት*

*መመሪያ ሁለት ከዚህ ቀጥል ሰባት የድርሰት ርዕሶች ቀርበዋል፤ ከሰባቱ ውስጥ ይበልጥ ሀሳባችሁን ሊትገልጹበት የሚያስችላችሁን ርዕስ በመምረጥ* 150-350 *በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ፃፉ::*

1.ስለ እናት ፍቅር

2.ስለ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር

3. ስለ ሕይወት ታርክ

4.ስለ ጎበዝ ገበሬ

5.ስለ ጎበዝ ተማሪ ተግባር

6.ስለሀገር ፍቅር

7.ስለ ወተት ጥቅም

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------::

## አባሪ ሶስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# የሂማንት፣የቋንቋ፣ጥናት ፣የጆርናልዝና ኮምዩንከሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**ለዲህረ ምረቃ ምርምር ለሚዘጋጅ ጽሁፍ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የፅህፈት ክሂል መፈተሻ ፈተና**

**ውድ ተማሪዎች ፡-**

*መመሪያ አንድ*

*የግል መረጃ ዕድሜ ---------------------የት/ቤት ስም----------------------የት/ቤቱ ዓይነት ሀ/የግል ለ/የመንግስት*

*መመሪያ ሁለት*

ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ተገብን የፍደላት ቅርፅ ፣ስርዓት ነጥብ ፣ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ፃፍ/ፊ/ (ዋጋ 10%)
የተሰጠ ሰዓት 15 ደቂቃ

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------::

## አባሪ አራት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

**የሂማንት፣የቋንቋ፣ጥናት ፣የጆርናልዝና ኮምዩንከሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

**ለ9ኛ ክፍል ተማርዎች የቀረበ የፅህፈት ክሂል ፈተና**

***ውድ ተማሪዎች ፡-***

***መመሪያ***

ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ስለእናት ፍቅር ጽፈህ/ ጽፊሽ/አምጣ/ጭ(15%)

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------

## አባሪ አምስት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂማንት፣የቋንቋ፣ጥናት ፣የጆርናልዝና ኮምዩንከሽን ኮሌጅ፤የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ውድ መምህራን

የዚህ መጠይቅ አላማ በአረካ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ወላይትኛ ቋንቋ አፊፊት ተማሪዎች በጽህፈት ክሂል የትኞቹ ተሸለው እንደምገኙ በማነፃፀር ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ ችግሩን፣በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

ስለዚህ ቃለ መጠይቁን በጥንቃቄ አድምጠው ተገብውን መልስ በመመለስ ቀና ትብብሩን እንድያደረጉ እጠይቆታለሁ፡፡በመሆኑም ውድ የሆነውን ጊዜ መስዋዕት በማድረግ ስለሚያደርጉልን ቀና ትብብር ሁሉ በቅድምያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የትምህርት ደረጃ-------------------የአገልግሎት ዘመን-----------------------

1.ለክፍሎ ተማሪዎች ስለአንቀጽ/ድርሰት አጻጻፍ ስያስትምሩ የግሏቸው ዘንድ ያደረጓቸውድጋፎች ምን ምን ናቸው፡፡

2.ተማሪዎች አንቀጽ/ደርሰት ስጽፉ ትክክለኛው የሆሄ ቅርጽ ለመጠቀም የሚያደርጉት ጥንቅቀ ምን ያህል ነው፡፡

3.ተማሪዎች ድርሰት /አንቀጽ በምጽፉበት ወቅት ተገብ ቃላትን በተገቢ ቦታ ስለመጠቅማቸው ያለዎት እምነት ምን ያህል ነው፡፡

4፣ተማሪዎች ድርሰቶቻቸውን/አንቀጾቻቸውን በሚጽፉበት ወቅት ስለቃላት አጠቃቀም ትኩረት እንዲያደርጉት በክፍልዎ ትምህርት አክለው ያስተማሩት ምን ምን ያካተተ ነበረ፡፡

5. የክፍልዎ ተማሪዎችን በየግላቸው በአንድ ርዕስ ዙሪያ አንቀጽ ሲጽፉ በአንቀጾቻቸው ጎልተውየሚታይባቸው ስህተቶች ምንድናቸው፡፡

# አባሪ ስድስት

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂማንት፣የቋንቋ፣ጥናት ፣የጆርናልዝና ኮምዩንከሽን ኮሌጅ፣የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፣ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

### ለድረሰት እርማት የተዘጋጀ መመዘኛ

### ውዴ መምህራን

ከዚህ በታች የተሰጠውን የእርማት መስፈርት ትርጉም በመጠቀም በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች ለይታችሁ በማውጣት የስህተቶቹን አይነትና ብዛት በተዘጋጀው ቅጽ ሊይ አስፍሩ፡፡ በመሆኑም ውድ መምህራን የተጣበበ ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ ለምታደርጉሌኝቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

| ተ/ቁ | የድርሰት ማረምያ መስፈርቶች | እጅግ በጣም ጥሩ | በጣም ጥሩ | አማካይ | ደካማ | በጣም ደካማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **ይዘት ፡** | | | | | |
| | -ስለርዕስ የተሟላ እውቀት ያዘለ፣ በደንብየተበራራ | | | | | |
| | -ስለርዕሱ መካከለኛ እውቀት ያዘለ | | | | | |
| | -ስለርዕሱ ምንም እውቀት ያላዘለ | | | | | |
| 2 | **አደረጃጀት፡** | | | | | |
| | -ርዕቱ የሆነ አገላለጽ የሚታይበት ፣ሀሳቦች በግልጽ የቀረበቡት | | | | | |
| | -በወጉ ያልተደራጀና እንደነገሩ የቀረበ፣ይህም ሆኖ ግን ዋናው ሀሳብ ተለይተው የሚታይበት | | | | | |
| | -ርዕቱነት የማይታይበት ሃሳቦች የተሚታቱበት /ያልተያያዙበት | | | | | |
| | -ምንም መልእክት የማያስተላለፍ፣ሀሳቦች የተሚታተበት | | | | | |
| 3 | **ቃላት** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | -በሳል የሆነ፣የተዋጣለት ቃላት፣የአባባሎች መረጣና አጠቃቀም የሚታይበት<br><br>-በበቂ ደረጃ፣አልፎ አልፎ የቃላት(አባባሎች ቅርጽ መረጣ አጠቃቀም | | | | | |
| | ስህተት ቢታይበት ምን ማለት እንደሆነ መገመት የሚቻለበት<br><br>-በውስን ደረጃ የቀረበ፣ቃላት መረጣና አጠቃቀም ተደጋጋም ስህተት የሚታይበት<br><br>- የቃላት ወይም አባባሎች አጠቃቀም እውቀቱ መጣም አነስተኛ የሆነ | | | | | |
| 4 | **የቋንቋ አጠቃቀም**<br><br>-ረቂቅ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም በተዋጣለት ሁኔታ የቀረበ ወዘተ<br><br>-የቋንቋ አጠቃቀሙ ተራ ሆኖ መለዕክቱ ግን በደንብ የሚተላለፍበት<br><br>- ረቀቂ ባለም ሆነ በተራ የቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የጎላ ችግር የሚታይበት<br><br>-በመሰረቱ የዐረፍተ ነገር አመሰራረት ሕግጋትን በወጉ ያለየ | | | | | |
| 5 | **ሥርዐተ አጻጻፍ**<br><br>-በሥርዐተ አጻጻፍ አጠቃቀሙ ብቃት ከፍተኛ የሆነ<br><br>-አልፎ አልፎ የሥርዐተ ነጥብና የሆሄያት ችግር የታየበት<br><br>-ተደጋጋም የሆነ የሥርዐተ ነጥብና የሆሔያ አጣጣል ችግር የምታይበት<br><br>-የሥርዐተ አጻጻፍ አጠቃቀም ብቃት የሌለው፣የሥርዐተ ነጥብ፣የፍደላት አጣጣል ችግር ጎልቶ የሚታይበት ወዘተ | | | | | |